Nile 8th year; publication No.3; March, 2022

# ናይል



Nile 8th year; publication No.3 March, 2022 ናይል 8ኛ ዓመት፣ ቁጥር 3፣መጋቢት 2014 ዓ.ም



ፕሮፌሰር ዳንኤል ቅጣው በኢትዮጵያ ቴክስታይልና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ፋሽን አዳራሽ ህዝበ ገለፃ ሲያካሂዱ

## “በሀገር ግንባታ የዩኒቨርሲቲዎች ሚና” በሚል ርዕስ ጉዳይ ሕዝበ ገለጻ ተካሄደ

በወንዳለ ድረስ

ፕሮፌሰር ዳንኤል ቅጣው “በሀገር ግንባታ ላይ የዩኒቨርሲቲዎች ሚና” በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ቴክስታይልና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት አዘጋጅነት የዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ እና ተጋባዥ እንግዶች በተገኙበት በኢንስቲትዩቱ ፋሽን አዳራሽ ህዝበ ገለፃ አድርገዋል፡፡




ህዝበ ገለፃውን በንግግር የከፈቱት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ፍሬው ተገኘ የኢትዮጵያ ቴክስታይልና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የራሱን ግቢ በመገንባት ሀገሪቱ በመስኩ የምትፈልገው የሰለጠነ የሰው ሀይል በማፍራት እና ችግር ፈቺ ምርምር በመስራት በአገራችን ቀዳሚ እና በተለይም በእድሜ እስካሁን በአገፍሪካ ተወዳዳሪ የሌለው አንጋፋና ግንባር ቀደም ተቋም መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ፕሬዚዳንቱ አክለውም በእለቱ ህዝበ ገለጻ ስለሚደርጉት ምሁር ሲገልጹ እንዳሉት ፕሮፌሰር ዳንኤል

ወደ ገፅ 3 ዞሯል

በውስጥ ገፆች

60ኛ አመትን አስመልክቶ የተካሄ ቴክኖሎጅ ቢዝነስ ሀሳብ ውድድር
ገፅ 4
Research and Development...
Page 7
በቴክኖሎጅ ዕውቀት የተፍታቱ እጆች...
ገፅ 9
የጉዞ ማስታወሻ
ገፅ 11
"ካንች የሚጠበቀውን ማድረግ ከቻልሽ...."
ገፅ 15

# ናይል

በኢንፎርሜሽን ስትራቴጂክ ኮሚዩኒኬሽን ም/ፕሬዘዳንት ጽ/ቤት
የውስጥ ግንኙነት እና ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የሚዘጋጅ ወርሀዊ ጋዜጣ

**ዋና አዘጋጅ**

ትዕግስት መኮንን
titibdu@gmail.com

**ግራፊክስ ዲዛይነር**

ትዕግስት መኮንን

**ዘጋቢዎች**

አለባቸው አለሙ

ሙሉጎጃም አንዱዓለም

ወንዳለ ድረስ

ሙሉጌታ ዘለቀ

ባንቹ ታረቀኝ

ሸጋው መስፍን

**አርታኢ**

ግርማው አሸብር

**ፀሀፊ**

መልሰው አደመ
አበባ ካሰው

**አምደኞች**

ደስታ ተከስተ
አስራት ደርብ

**ስርጭት**

አለነ ጋሹ

አልማዝ አምበሉ

ኑኑሸት ምትኩ

ትርንጎ ወለላው

ወርቅነሽ አበባው

ቀራለም አድማሱ

**ፎቶግራፈሮች**

ታምራት አታላይ

በሪሁን ታረቀኝ

ቤተልሄም ወርቅነህ

አገሬ ዘለቀ

**ሾፌር**

ላመስግን ጫኔ

ፋንታሁን አንሙት

አባይ ማተሚያ ቤት ታተመ፣ መጋቢት
2014 ዓ.ም

www.bdu.edu.et | www.facebook.com/bduethiopia | www.twitter.com.bdu.et | +251583206059




**Motto:**

**Wisdom at the source of the Blue Nile**

Vision:

**BDU aspires to be one of the leading research-intensive universities in Africa and the first choice in Ethiopia by 2030.**

Mission:

**Promote advanced research and innovation on the basis of the country's requirements;**
**Produce graduates with relevant professions and necessary competences (knowledge, skills and attitude) to respond to the national labor market requirements to eventually ascertain the global competitiveness of the country;**
**Improve lives through evidence-based and transformative community engagement;**
**Enhance demand-driven and problem solving technology transfer**

# ርዕሰ-አንቀጽ

## የኢትዮጵያ የወደፊት ህልውና በተማሩት ዜጎቿ እጅ ውስጥ ነው!

የአንድ ሀገር ህልውና የሚቀጥለው በተማሩ ዜጎቿ ጥረትና ብልሃት መሆኑን አሁን ያለንበት የውድድር አለም ማሳያ ነው። በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያዎቹ ዓመታት ገደማ ዘመናዊነት በኢትዮጵያ ሰማይ ስር እንዲያብብ ፣ የምስራቅና ምዕራቡን ዓለም ስልጣኔ የቀመሱ ዜጎች ዋነኛ የአገር ምስረታ አጋፋሪ ሲሆኑ አበጃችሁ፣ ግፉበት ብለን ተባባሪ ስለሆንን ኢትዮጵያዊያን ካበረከቷቸው የቴክኖሎጂ እመርታዎች ባሻገር የውጭ ሃገራት ፍልስፍናና ቴክኖሎጂ ተቋዳሽ ሆናለች።

ዛሬም ከጥቀት አገር በቀል አበርክቶዎች በስተቀር ምዕራባዊያን የተጠቀሙበትን ድንጋይ ካልደረደርን፣ ስራዎቻችን በምዕራባዊያን ሚዛን ካልሰፈርን እውቀት የማይመስለን ምሁራን ተበራክተናል። ይህ አስተሳሰብ በትህርት ስርዓታችን ሳይቀር እውነት ሆኖ እናገኘዋለን። ከሃገር በቀል እውቀት ይልቅ የባህር ማዶ ለሆኑ ነገሮች ሁሉ ጊዜና ሃብታችንን ስናፈስ እንስተዋላለን። ይህ አካሄድ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ታዳጊ እና ጥንታዊ ነባር ባህልና ጥበብ ባለቤት ለሆኑ አገሮች ከባድ ድንጋይ ባንገት አስሮ ቁልቁል እንደመወርወር ይቆጠራል።

ኢትዮጵያ በስነ-መለኮት፣ በሃገረ መንግስት ምስረታ፣ በዕፅዋትና እንስሳት ልማት፣ በፖለቲካ እና በኪነህንጻ ጥበብ ቀዳሚ ሃገር የነበረች እና አሁንም በብዙ ዘርፎች ልቀው በሚታዩ ትጉህ ዜጎቿ የእድሷ አለመታጠፍ አመላካች ናቸው።

ጥንታዊ ትምህርትና ጥበብ ከቤተ እምነቶች ወቶ ቤተ መንግስት ደጅ ከደረሰ ጀምሮ የሃገራችን ዜጎች የራሳቸውን መሰረት ከማጥናት ይልቅ የባህር ማዶ ጥበብ በመናፈቅ ቀልባቸው ተነጥቋል። መሰረተ ነገራችን ሁሉ በሐገረኛው ማማር/መዋብ ሲገባው የጥበብ ሁሉ መልካምነት መመዘኛ የባህር ማዶ ብቻ አድርገነዋል። ጥበብን መማርና መናፈቅ የሌሎችን ማድነቅ የጥንት የኢትዮጵያዊያን ሊቃውንት በጎ ነገራቸው ስለሆነ አስነዋሪ ነገር የለውም። የራስን አንቋሾ ንቆና ተጸይፎ በሰው ወርቅ ለመድመቅ መሞከር ግን አገርን ከነበረ ክብሯ እና መንበሯ ማውረድ ነው!

ታዲያ ዋናው ቁም ነገራችን ማጠንጠን ያለበት የሌላውን አለም ጸጋ የራስ ማዳበሪያ ማድረግ እንጅ የራስን ጥሎ በሌሎች ለመድመቅ መሞከር አበው ሲተርቱ እንደሚሉት የሰው ወርቅ አያደምቅ ነውና ስለራሳችን መጠየቅ፣ ማወቅ፣ ማፍለቅና መድመቅ ይኖርብናል። ይህ ሲሆን ከየቤተ-እምነቶቻችን አካባቢ አገሬን ብሎ ያደፈጠው ነባር ጥበባችንና የአኗኗራችን መልክ ሁሉ መፈተሽ ፣ በየባለሃገሩ ቤት ያለውን ሃገረሰባዊ ጥበብ ማየትና መመርመር፣ የቀደሙ የአገራችንን ሰነዶች መፈተሽ ፣መግለጥ ፣ማጥናትና ለአሁኗ አገራችንና እጣ ፋንታችን መውጫ መንገድ ማስመሪያ ማድረግ ለነገ የሚባል ተግባር አይሆንም።

ምሁራን በዚህ ጎዳና ላይ ራሳቸውን ማስቀመጥ ከጀመሩ ከራሳቸው ጋር መታረቅ፣ ሀገራቸውንም ከራሷ ተራቁታ በሰው ወርቅ ካሸበረቀችበት የውሸት አብለጭላጭ ውበት ነጻ ማውጣትና ነገዋን በራሷ መሰረት ላይ እንድትተክል ያደርጓታል። በዚህም ነገዋ እየፈካ፣ አዲስ ትውልድ በአዲስ ተስፋ እየተተካ የአገራችን ህልውና ከፈተና ወጥቶ ወደ እድገት ማማ ማቅናት ይጀምራል።

## "በሀገር ግንባታ የዩኒቨርሲቲዎች ሚና"

ከገፅ 1 የቀጠለ

ሀገራችን ካሏት ፀጋ ካላቸው ሰዎች አንዱ እና በሙያቸውም ለሃገራቸው መፅሀፍ የፃፉ በተለይም ባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በሁለት እግሩ ይቆም ዘንድ የረጅም ጊዜ አገልግሎት የሰጡ አንጋፋ ሳይንቲስት መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ፕሮፌሰር ዳንኤል በገለፃቸው ዩኒቨርሲቲ የምናስለጥናቸው ተማሪዎች ለኢንዱስትሪው ተፈላጊ ስለመሆናቸውና የትምህርት ጥራቱ ምን ያህል ነው በሚለው ነጥብ ላይ መስራት እንዳለበት ተቁመዋል።

አያይዘውም እንደ ሃገር ለውጥ እንድናመጣ ከተፈለገ የሰው አዕምሮ ላይ በመስራት የቴክኖሎጂ ሽግግር የምንለውን፤ እቃዎችንና አገልግሎቶችን ለማምረት እና ለመጠቀም የሚያገለግል የእውቀት፣ የክህሎት፣ የልምድ እና የአደረጃጀት ስርዓቱን ማሸጋገር ስንችል መሆኑ ቢታወቅም ይህን ተግባራዊ ማድረግ ላይ ብዙ እንደሚጎድል ተናግረዋል።

ፕሮፌሰሩ ስለስራ ክቡርነትና ተጠያቂነት ሲተነትኑ እንዳሉት

‹‹አንድ ሰው ተጠያቂ የሚሆነው ስላጠፋው ጥፋት ብቻ ሳይሆን ማድረግ ሲገባው ባላላደረገው ነገር ተጠያቂ መሆን አለበት›› ብለዋል፡ በዚህም የአገራችን ዩኒቨርሲቲዎች በአብዛኛው ተጠያቂ መሆናቸውን ስለመሆናቸው በማስረጃ ገልጸዋል።

በህዝበ ገለጻው የዩኒቨርሲቲው አመራሮች፣ መምህራንና አስ/ሰራተኞች፣ ተማሪዎችና ተጋባዥ እንግዶች ተገኝተዋል።

ከተሳታፊዎች በቀረበው ህዝበ ገለጻ ጥያቄና አስተያየት ተነስቶ በፕሮፌሰሩ ምላሽ ተሰጥቶ የመርሃ ግብሩ ፍጻሜ ተጠናቋል



ፕሮፌሰር ዳንኤል ቀጣው ከህዝበ ገለፃው በኋላ ከዩኒቨርሲቲው የበላይ አካላት ጋር የተቋሙን ወርክሾፖች ሲጎበኙ

# ሠሞነኛ

ይህ አምድ ከዜናዎች በተጨማሪ ወቅታዊ ጉዳዮችን መነሻ በማድረግ ሀተታዊ ፅሁፎች ይቀርብበታል




## የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ 60ኛ ዓመትን ምክንያት በማድረግ የቴክኖሎጂ ቢዝነስ ሐሳብ ውድድር ማስጀመርያ ፕሮግራም ተካሄደ

በታምራት ሰሙ

በባ/ዳ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጅ ተቋምየውጭ ግኑኝነት አስተባባሪ

በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጅተቋም አዘጋጅነት በተካሄደው ፕሮግራም ላይ እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት የመክፈቻ ፕሮግራም ያደረጉት የባሕር ዳር ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ሳይንቲፊክ ዳይሬክተር ዶ/ር ሠይፉ አድማሱ የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ ለባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ 60ኛ ዓመት በዓል አከባበር ድምቀት የሚሆን ውድድር በማካሄድ ታላላቅ የሆኑ የቴክኖሎጅ የፈጠራ ውጤቶችን እውን ለማድረግ ታስቦ የሚካሄድ እንደሆነ ገልጸዋል::

ይህም በተደራጀ መልኩ ከሄደ እንደ ዕቅድ እስከ እ.ኤ.አ. 2025 ራሳቸውን የቻሉ እና ማሕበረሰቡን የሚያግዙ ድርጅቶችን ማቋቋም ያስችላል ብለዋል:: የኢንስቲትዩቱ ምክትል ሳይንቲፊክ ዳይሬክተር ዶ/ር መኳንንት አገኘሁ በበኩላቸው ቴክኖሎጂ ነክ የሆኑ የሥራ ፈጠራ ሐሳቦችን ከሥራ ክህሎት ጋር በማጣመር ኢንስቲትዩቱ ረጅም ያለመ እንደመሆኑ መጠን BiTec ወጣት ኢንትርፕሬነሮችን ለመፍጠር እና ለማገዝ የተቋቋመ ነው:: ከዚህም ጋር ተያይዞ የተለያዩ Hackathon እና Makaton ጨምሮ የተለያዩ ፕሮግራሞችን ማካሄዱ ጠቁመዋል::

በዚህም 3 የሚሆኑ ቡድኖች በሐገር ዓቀፍ ደረጃ በሚዘጋጀው Bruh National Competition ውድድር በመሳተፍ 2ኛ 5ኛ እና 8ኛ መዉጣታቸውን ገልጽዋል::

ከተውዳደሩት መካከል የAgelgil Eco Packaging እና Ray cosmetics መሥራች የሆኑት ወ/ት አፎሚያ እና ወ/ት ራውላ ሥራቸውን ለዓዲሶቹ ሠልጣኞች አቅርበዋል::

በዚህም የነበረባቸውን ፈተና እና የገጠማቸውን ችግር በመግለጽ አዳዲስ ሠልጣኞች ረጅም አቀደው ከፊት በሚገጠማቸው እንከንእንዳይደናቀፉም ምክራቸውን ለግሰዋል::

የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጅ ተቋም Makerspace አስተባባሪ ወ/ት ቤዛወርቅ በበኩላቸው ባ/ዳ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጅ ተቋም የአፍሪካ Makerspace አባል መሆኑን በመግለጽ ከግለሰብ ጀምሮ ከተለያዩ ተቋማት እርዳታ እንዳልተለየው ገልጸዋል::

ይህም በሐገር ደረጃ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ደረጃ ለውድድር የበቃ ሥራ መቀረቡን በመጠቆም በመጪው ግዜ በሐገር ደረጃ አሸናፊ የሆኑት Agelgil Eco Packaging እና Ray cosmetics በአፍሪካ ደረጃ የገቡበትን ውድድር አሸናፊ እንደሚሆኑ እምነታቸውንገልጸዋል::

ዶ/ር በረከት በበኩላቸው የHuman Centered Design (HCD) ምንነት ለታዳሚው ያብራሩ ሲሆን ከጊዜያት በፊት እንደነበረው ባህላዊው የአሰራር ዜዴ ሳይሆን ተጠቃሚዎች በምርጫ የታጀቡ እንደመሆናቸው መጠን ማርካት የሚችል እና የተሻለ ሥራ አስፈላጊ ይሆናል በማለት የወ/ት ራውላን ሐሳብ ባጠናከረ መልኩ ሰዎች የሚሰሯቸውን ሥራዎች ከተጠቃሚው አንጻር ማድረግ አስፈላጊ ምሆኑን ገልፀዋል::

ሥልጠናው ለ 4 ቀን የሚቆይ ሲሆን በሚያዝያ 7 ቀን 2014ዓም የመስክ መልከታ እንደሚኖር ተገልጿል:: በውድድር ውስጥ 53 ተማሪዎች በ12 የቢዝነስ ቡድኖች የተዋቀሩ ሲሆኑ በተዘጋጀው መስፈርት መሠረት እንደሚመዘኑ ታውቋል::

## በቴክኖሎጂ ዕውቀት የተፍታቱ እጆች.... ከገፅ 9 የቀጠለ

ወደ ገበያ ለመውጣት ከታሰቡ እቅዶች መካከል፤ ከሚመለከተው የመንግስት መስሪያ ቤት ጋር በመነጋገር የመሥሪያ ቦታ፤ የንግድ እና የስራ ፈቃድ ማውጣት እና ድርጅቱን /ካምፓኒውን / ለማቋቋም እና ለማንቀሳቀስ የሚያስችል ገንዘብ በድጋፍ ማፈላለግ እና ማቋቋም ምረቱን አምርቶ ወደ ገበያ ለማውጣት እቅዶችን ይዘው እየሰሩ መሆኑን ተናግረዋል::

የፈጠራው ባለቤት የሆኑ ተማሪዎቹ በስራው ሂደት ላይ ከነበሩ ተግዳሮቶች መካከል ሙከረውን ለመስራት የሚያስችሉ ማሽኖች እና ጥሬ ዕቃዎችን ለማግኘት በተለያዩ ምክንያቶች ረጅም ጊዜ መውሰድ እና አንዳንድ የቡድን አባላት ፕሮጀንክቱን ትቶ መውጣት እና የመሳሰሉት ተግዳሮቶች እንደነበሩ ጠቅሰዋል::

እንደሚታወቀው ሃገራችን በርካታ ምርቶችን ከውጭ በማስገባቷ ተከታታይ እድገትን ለማምጣት የሀገር በቀል አውቀትን ባለመጠቀማችን የዕድገታችን ማነቆ መሆኑ ይነገራል::

ይህ የሆነውም ሃገራችን የተማረና የንግድ ሃሳብ ያለው ሰው አጥታ ሳይሆን አብዛኛው ተቀጥሮ መስራትና ብዙ ውጣ ውረዶችን ወይም መሰናክሎችን አስቀድሞ ከመፍራት የሚመጣ መሆኑን ጥናቶች ያመለክታሉ:: የተማሪዎች የመመረቂያ ጽሁፍ (Thesis) ከችግሮች በመነሳት የመፍትሄ ሀሳቦችን የሚያመላክቱ እንዲሆኑና የተለያዩ ልምድ ያላቸው ሰዎችን በማማከር ለሀገር የሚጠቅም ትልቅ ፋይዳ ያለው የምርምር ስራ ማበርከት እንደሚችሉ ተማሪዎች አስረግጠው ይናገራሉ::

በዚህም ሂደት ዩኒቨርስቲው እስካሁን ተንከባክቦ፣ አቅፎና ደግፎ ለዚህ ደረጃ ማብቃቱን ተማሪዎቹ አመስግነው እውቀታቸውን ተጠቅመው የፈጠራ ስራቸውን ወደ ምርት በማስገባትና ወደገበያ እንድናቀርብ የሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶችና አጋር ድርጅቶች ጋር በጋር ለመስራት የመስሪያ ቦታና መነሻ ካፒታል (የስራ መጀመሪያ ብር) ቢመቻቹላቸው ፍላጎታቸው መሆኑን ይናገራሉ::

ሌሎች የሚመልከታቸው የመንግስትም ሆነ የግል ተቋማት ምርቱን በስፋት ለማምርት በሚደረገው ሂደት ውስጥ ከጎናቸው ሁነው እንዲያግዟአቸው ይጠይቃሉ::

በአሁኑ ሰዓት ሀገሪቱ በብዙ መንገድ ኢኮኖሚዋ እያሽቆለቆለ በመምጣቱ ከችግሮቻችን ማነቆ ለመውጣት ሙሁራን ከህብረተሰቡ ችግር በመነሳት ለችግሮቹ የመፍትሄ ሀሳብ የሚሆኑ የምርምር ስራዎችን በመስራት የህዝቡን ችግር ማስወገድ አለባቸው:: ሁሉም የትምህርት ተቋማት በቻሉት መጠን ለሀገር የሚጠቅም ዜጋ ከማብቃት አንፃር ተምሮ የመንግስት ተቀጣሪ ሳይሆን ስራ ፈጣሪና ተመራማሪ እንዲሆኑ ተማሪዎችን መሰረት ያደረገ የትምህርት አሰጣጥ መርህ ቢከተሉ




## “ካንች የሚጠበቀውን ማድረግ ከቻልሽ...

ከገፅ 15 የቀጠለ

ለኛ የከፈሉትን መስዋትነት ሁሌም መዘንጋት የለብንም::

እኔ ሁሌ ለጓደኞቸ እንደ ምሳሌ የምነግራቸው በ12ኛ ክፍል ውጤቴ ያዘኑትን ቤተሰቦቸ የሆነ ቀን አስደስታቸዋለሁ እያልኩ እነግራቸዋለሁ:: ቤተሰብን እና ሀገራችን እያሰብን ከተማርን ከዓላማችን ዝንፍ እንላለን ብየ አልገምትም::

ከመደበኛ ትምህርት ባሻገር በዩኒቨርሲቲ ቆይታየ በሌሎች ነገሮች ላይ ተሳት አደርጋለሁ:: በበጎ ፈቃድ ክበበ በዓላት ሲደርስ ጫማ በመቀባት፣ ከህብረተሰቡ ብር በመሰብሰብ ለተቸገሩ ለመርዳት ሞክረናል:: ከዚህ ባለፈ የቀን ተቀን ውሏችን ሆስፒታል አካባቢ እንደመሆኑ ተኝተው ለሚታከሙ የማህበረሰቡ አካላት፤ ቤታቸው ቢሆኑ ሊያገኙት የሚችሉትን እንደ ቡና ማፍላት፣ ምግብ ማብላት እናደርግ ነበር:: ሌሎችን ከመርዳት ባለፈ በዕርስ በርስ ግንኙነታችን የገባው ላገባው በመረዳዳት ነበር ያሳለፍነው ትላለች::

ሌላው ታች ክፍል ላይ ለመምህራኖቻችን ክብር ነበረን፤ ግቢ ላይ የምመለከታቸው ተማሪዎች ግን ለዚህ ብዙም ትኩረት አይሰጡም:: ይህ ደግሞ ተማሪውን መልሶ የሚጎዳ በመሆኑ መምህራኖች የሚሉንን መስማት ይኖርብናል::

በተጨማሪም የኮረና ቫይረስ ወረርሽኝ እና የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ በፈጠረው ጫና እና የትምርት ጊዜው መቆራረጥ ከፍተኛ ጫና እንደፈጠረባት እና ፈታኝ እንደነበር ታስታውሳለች::

የትምህርት ስርዓቱን ላይ አስተያየት ስትሰጥ በተለይም ከዩኒቨርስቲ በታች ያሉ የትምህርት አሰጣጥ ከተግባር ይልቅ በንግግር ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ወደ ዩኒቨርስቲ ለሚመጡ ተማሪዎች ሁሉም ነገር አዲስ ይሆንባቸዋል:: ሁሌም እንደማስበው የትምህርት ስርዓታችን ተግባር ተኮር ሲሆን ከአዕምሮ ስለማይጠፋ አይረሳም ትላለች::

በመጨረሻም ለዚህ ስኬት ያበቋትን ስታመሰግን ከፈጣሪ ቀጥሎ ያለ አባት አሳድጋ ያስተማረቻትን እህቷን ያመሰገነችው ራሄል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን እንድትከታተል የረዳቻትን አክስቷ በማስታወስ እንደ እናት እና እህት በመምከር ትልቅ ውለታ እንደሰራችላት በመግለፅ አመስግናለች:: በዚህም አንዳንዴ በፊት በነበረው ውጤት ስተክዝ‹‹ ሰው ከውድቀቱም ይማራል፤ “ካንች የሚጠበቀውን ማድረግ ከቻልሽ ስኬትን ታገኛለሽ›› እያለች እዚህ ያደረሰችኝን አክስቴን እና ግቢ ውስጥ ያሉ መምራኖችን አመስግናለች::

> ”ቤተሰብን እና ሀገራችን እያሰብን ከተማርን ከዓላማችን ዝንፍ እንላለን ብየ አልገምትም።”
>
> ራሄል ድርብ ወርቅ

# Research and Development... Continued from page 7

The commitment of allocating a small share of money from the national GDP to research and development will have an enormous impact on higher education institutions at the same time.

Research and development in the eye of Ethiopian public University
The Ethiopian government uses four budget item descriptions to run the higher education program. These budget characteristics are fundamentally linked with the missions of the universities. These are administration and management (AM), Teaching and Learning (TL), Research and Development (RD), and Consultancy and Community Services (CS). Administration and management costs deal with all functions concerned with the administrative wing of the universities. These costs include but are not limited to administrative personnel's salary, other benefits, and the cost of office utilities, stationery, and maintenance. On the other hand, the cost of teaching and learning mainly covers the salary of academic staff and other benefits and all other expenses to run the teaching-learning processes. The research and development cost covers research undertaking, publications, dissemination, knowledge production, knowledge transfer, etc. Finally, consultancy and community services costs include all the consultancy issues and activities geared to community engagement practices. The Ethiopian government allocates a recurrent budget as a block grant to all universities. The University's responsibility is to prioritize its activities and assign budgets for each budget item accordingly.

By default, administration and management and teaching-learning budget categories will take a sheer amount of money since both expenses include administrative and academic personnel salaries.


However, the two budget categories mentioned above often take a large budget share; universities shall balance the other budget categories to ensure each University's mission receives relatively equal attention. Yet, the existing data do not assure such a claim. To support my argument with empirical evidence, let us see all public universities' last six years (from 2015/16 to 2020/21) budget allocation trends. These budget data are the total budget that universities receive from the government. It does not include the budget that universities subsidize this core mission from their internal revenue.

Once the universities receive a lump sum of finance from the government, it is the University's internal decision to decide on how to distribute its budget among different programs and operational activities. One crucial issue that we can allude to universities' budgeting trend for their core missions is looking at the amount of money allocated for each core mission.

In this regard, we can see some irregularities among the budget item categories. There are also anomalies among public universities to treat research and development missions. Research and development are one of the core missions that should get equal attention to other missions to enhance the University's knowledge production, innovation, and dissemination capabilities.


The paradox between enrollment trends of Postgraduate programs and R & D
To show some enrollment trends of postgraduate students in Ethiopian public universities, I just wanted to see nine-year data obtained from the then Ministry of Science and Higher Education (MoSHE, 2020) documents. As can be seen from the diagram, the number of postgraduate students (PhD & MA/MSC) have been rising high with an average growth rate of 22.2%. The postgraduate program, by its nature, is cost-intensive, meaning it requires an immense amount of money for research and development activities. Such enrollment trends tell university leaders or higher education decision-makers to search wide-range sources of resources to help finance graduate programs. However, many public universities' experiences showed that they rely on the government funding system to meet their needs. Due to such limited financial sources, the research and development program's budget allocation has become meagre, less than 4% of the overall recurrent budget.

*Figure 1. The budget share of R & D core activity in all public universities from 2015/16 to 2020/21*




*Source: MoFEC (2021)*

The table shows that while the percentage of the budget given to research and development has increased marginally over the last six years, it remains tiny and last (average of less than 4%) compared to other budget categories and core missions. Therefore, research and development are the most important but the least prioritized mission in Ethiopian public universities. The six consecutive years' budget allocation trends entail important messages to university decision-makers to rethink it.




*Source: MoE (2020)*

To conclude, what can Bahir Dar University learn from this experience? In the subsequent publication, I will continue my data-driven assessment of Bahir Dar University's experience and attempt to provide possible way outs.

# እጅ ከምን

በዚህ አምድ የዩኒቨርሲቲው ባልደረቦች እጅ ከምን ስንል አለን የምትሉት ለአንባቢ የሚበቃ ፅሁፍ ይስተናገድበታል

# Research and Development: The least prioritized mission in Ethiopian public universities

By Asrat Derb
PhD candidate in Higher Education Leadership and Management( Email: asrat.dereb@bdu.edu.et)

Prelude: This section is devoted to sharing ideas, arguments, and philosophies of higher education institutions, notably universities. More specifically, academic discourse such as organizational theories, leadership and management practices that are linked to the systems' core missions will be conferred. Therefore, this academic discourse aims to share theoretical and philosophical underpinnings substantiated with empirical evidence.

This empirically based reflection aims to show the current state of Ethiopian public universities' research and development core mission. Research and Development (R & D) refers to a university's activities to innovate and create new products and services.

A university that wants to remain competitive should gear all its efforts toward innovation so as to produce high-quality products and services. Such results could be possible if research and development become an institution's culture.

It is now widely understood that a country must acquire high-level skills and competencies, as well as scientific research, innovation, and technology development capabilities, to succeed in the knowledge economy.

Higher education, and universities, in particular, are regarded as critical agents in delivering these knowledge capabilities for development, based on their traditional role of producing, applying, and disseminating knowledge and educating the next generation of knowledgeable and suitably qualified workers. Cognizant of the importance of research and development for the country's overall development, many countries give due emphasis and make it their priority goal.

Governments, above all, provide this mission to higher education institutions, though other institutions are also responsible. As a result, research and development are now one of the three core missions of higher education institutions, particularly universities.

## World trends:

Lesson from other countries

As a World Economic Forum indicated, investment in research and development is essential to national economies and plays a significant role in enhancing the Growth Domestic Products (GDP).

Countries that allocated a relatively high share of the budget from the national GDP for research and development have registered better in the national development index. For instance, let us look at the world and African countries' experiences regarding the R & D budget share from their respective national GDPs. Some countries spend a large proportion of their GDP on research and development activities. Israel, South Korea, Switzerland, Sweden, and Japan are the top five countries that spend the most on research and development. Table 1 shows different countries' trends in sharing R & D from the country's GDP.

*Table 2. African countries spend the most on research and development*

| Rank | Countries | Year | Share of GDP on R & D |
|---|---|---|---|
| 1 | South Africa | 2017 | 0.82% |
| 2 | Egypt | 2018 | 0.72% |
| 3 | Burkina Faso | 2017 | 0.61% |
| 4 | Tunisia | 2018 | 0.6% |
| 5 | Algeria | 2017 | 0.54% |
| 6 | Mauritius | 2018 | 0.35% |
| 7 | Mali | 2017 | 0.29% |
| 8 | Ethiopia | 2017 | 0.27% |
| 9 | Burundi | 2018 | 0.21% |
| 10 | Gambia | 2018 | 0.07% |

*Source: World Bank (2021)*

## African countries' status

According to the world bank data, the top five African countries that spent a high share of R & D from their GDPs are South Africa, Egypt, Burkina Faso, and Tunisia. Ethiopia spent 0.27 % of its GDP on research and development activities. In comparison to other Western and Asian countries, African countries fall behind. All African countries set aside less than 1% of their GDP for research and development. Such data raise a number of questions for policy formulators and decision-makers.

*Refere Table 2. above*

**Table 1. World countries spend the most on research and development**

| Rank | Countries | Year | Share of GDP on R & D |
|---|---|---|---|
| 1 | Israel | 2018 | 4.95% |
| 2 | South Korea | 2018 | 4.81% |
| 3 | Switzerland | 2017 | 3.37% |
| 4 | Sweden | 2018 | 3.34% |
| 5 | Japan | 2018 | 3.26% |
| 6 | Austria | 2018 | 3.17 |
| 7 | Germany | 2018 | 3.09% |
| 8 | Denmark | 2018 | 3.06% |
| 9 | United States | 2018 | 2.84% |
| 10 | Belgium | 2018 | 2.82% |
| 13 | China | 2018 | 2.19% |

# ባህረ_ሃሳብ

ይህ አምድ የተለያዩ የሀሳብ ልዩነቶችን የሚያንፀባርቁ ፅሁፎች፣ ትዝብቶች እና ክርክሮች ይቀርብበታል

## ‹‹ጊዜ ወርቅ አይደለም ፤ህይወት ነው!!››

በአለባቸው አለሙ

የአንድ ግለሰብም ሆነ ሀገር ስኬታማነት እና የህይወት ጥራት ከሚመዘንባቸውና ከሚለኩባቸው ጉዳዮች አንዱና ዋናው የጊዜ አጠቃቀም ሁኔታ ነው፡፡ በዚህ ዙሪያ ብዙ ሲባል እንሰማለን ምናልባትም እኛም ልናስበውና ልንናገረውም እንችል ይሆናል::

አብዛኞቻችን ኢትዮጵያውያን የጊዜ አጠቃቀም ችግራችን በጣም ሰፊ ነው፡፡ ለዚህም ስለጊዜ አጠቃቀምና ስለ ሰው ልጅ ግንኙነት ቀጥሎ የሰፈረው የከበደ ሚካኤል ግጥም ብዙ ነገር ይነግረናል፡፡

ካልተሳፈሩበት ቶሎ
ተሽቀዳድሞ ፤

ጊዜ ታክሲ አይደለም
አይጠብቅም ቆሞ::

ጊዜ እንደ ታክሲ ቆሞ የማይጠብቀንና ካልተጠቀምንበት ጥሎን የሚያልፍ መሆኑን ባለመገንዘብና ችላ በማለት ብዙ ነገሮችን በጊዜአቸው ሳናከናውን እንቀርና እንቆጫለን፡፡ አንዳንድ ጊዜ ‹‹ጊዜው አልመሸልኝ ብሎ››፣ ‹‹ጊዜ ማሳለፊያ›› ወዘተ. የሚሉ አባባሎች ለጆሯችን ቅርብ ናቸው፡፡ ነገር ግን ጊዜ ወርቅ ነው ተብሎ በቁስ ከሚገለጸው በላይ አሁን አሁን ጊዜ ህየይወት ነው እየተባለ ነው፡፡

ለስብሰባም ይሁን ለሌላ ጉዳይ በተቀጣጠርንበት ጊዜ አክብረን የመገኘት ልምድና ባህላችን በጣም ክፍተት ያለበት ነው::ለዚህም አይደል አይ የአበሻ ቀጠሮ እየተባለ የሚነገረው፡፡ ለመሆኑ አበሻን ማን ነው ጊዜ አታክብር ብሎ የበየነበት፡፡

ለአህጉርና ለአገራትም የጊዜ አጠቃቀም ደረጃ ወጥቶላቸው የአፍሪካ ጊዜ፤ የአውሮፓ ጊዜ፤ በተመሳሳይ እገሌ ጊዜ አክባሪ ነው፤ እገሌ ስለጊዜ ግድ የለውም ወይም ማርፈድ ይወዳል በቀጠሮ ሰአት በጊዜው አይገኝም እንዲሁም እነእገሌ የጠሩት ስብሰባ ጊዜ ይከበርበታል፤ እነ እገሌ የጠሩት ስብሰባ እነርሱም ሆነ ተሰብሳቢዎችም ጊዜ የማያከብሩና የጊዜ ዋጋ ያልገባቸው ናቸው ይባላል፡፡

ቀጠሮ የማያከብሩ አርፋጆችን ሰበብ አስባብ እየተፈጠረ እንጠብቃቸው በሚል ሰአት አክብረው የተገኙት ይቀጣሉ፡፡ ዛሬ በሰአቱ የተገኙት ነገ በሰአቱ እንዳትመጡ እየተባሉ ቃል በሌለው ድርጊት ሲበረታቱ ይታያሉ፡፡

አ ር ፍ ደ ው የ ሚ መ ጡ ት ም የእነርሱንም ሆነ በሰዓቱ የተገኙትን እንዲሁም በዘልማድ ላደረጉት ብልሽትና መጥፎ ስነ-ምግባር አይወቀሱም አይገሰጹም፡፡

በጊዜ ጉዳይ እነዚህን የመሳሰሉትን እናያለን፤ እንሰማለን፤ እናወራለን፤ ከጊዜ የተነሳም ማንነትን በተመሳሳይ አገልግሎትንም፤ እንመዝናለን በውስጡም የወደፊት ውድቀታቸውንና አሁን ያሉበትን እንገልጻለን፡፡

እንደሚታወቀው በጊዜው ያልሆነ ተግባር፤ እቃ፤ ማንነት እና ሌሎችም ከጥቅሙ ይልቅ ኪሳራው፤ ጉዳቱና ውድቀቱ ይበዛል፤ ተቀባይነቱም በጊዜው እንደሚሆነው እንዳልሆነ በእለት ከእለት እንቅስቃሴአችን የምንገነዘበው ነው፡፡ ጊዜ ጥልቅ ሚዛን ነው፡፡

በተለይ አሁን ባለንበት ዘመን አንድ ሰው ጊዜውን ሰጠ ማለት ህይወቱን ሰጠ ማለት ነው ብንል ማጋነን አይሆንም፡፡

ምክንያቱም የብዙ ነገር ለውጥ እንደድሮው አዝጋሚ ሳይሆን እንደምናየው ቅጽበታዊ እንደሆነ ሁሉም የሚረዳው ነው:: ስለዚህ በጊዜው ተጠቅመን መስራትና የጊዜ አጠቃቀማችንን እያስተካከልን እድሎችን መጠቀም ካልቻልን ዘወር ስንል አናገኘውም::


በዚህም ምክንያት ለህይወታችን አስፈላጊ የሆኑ ዋና ዋና ነገሮችን እናጣቸዋለን፡፡ ህይወት በኪሳራ ምዕራፍ ይሞላል፡፡ በዚህና በሌሎች ምክንያቶች ሰው ጊዜ ሲሰጥ ወይም ጊዜውን ጥቅም በሌላቸው ጉዳዮች ላይ ሲያጠፋ የህይወቱን ትልቅ ነገር እንዳጠፋና ህይወቱን እንደሰጠ መረዳት ይቻላል፡፡

ሰዎች በእለት ከእለት ኑሮአችን የሚያስፈልጉን ብዙ ህይወት የሌላቸው ነገሮች አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ዋነኞቹ ህይወት ሳይኖራው ህይወት ተብለው የሚጠሩት ውሃ፤ ምግብ እና አየር ናቸው፡፡ እነዚህ ነገሮች ሰው በህይወት ለመኖር የግድ አስፈላጊ በመሆናቸው ነው ህይወት ናቸው የሚባሉት::

የሰው ልጅ እነዚህን ዋነኛ ነገሮች ከህይወቱ ቢያጣ በህይወት የሚቆየው በጣም ለአጭር ወይም ለጥቂት ጊዜ ነው፡፡ ለምሳሌ ሰው አየር ቢያጣ ከአምስት ደቂቃ በላይ አይቆይም፡፡

ምግብ ቢያጣ ደግሞ በህይወት የሚቆይበት ጊዜው ከ40 እስከ 45 ቀናት በላይ እንደማይቆይ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ነገር ግን የመኖር ጊዜው ቢያልቅ ያለምንም ማመንታት በቅጽበት ሙት ወደ መሆን ይቀየራል፡፡ ይህም ማለት ጊዜ አለቀ ማለት ህይወት አለቀ እንዲሁም ጊዜ አለህ ማለት ሕይወት አለህ ማለት ነው፡፡

### ስለጊዜ አጠቃቀማችን ማወቃችን



| | |
|---|---|
| · | ስራችንን በውጤታማነት እንድንሰራ ይረዳናል፤ |
| · | ከሕይወት ዘመን ግብ ላይ ለመድረስ ይረዳናል፤ |
| · | ለድርጊቶች አፈጻጸም ቅደም ተከተል እናወጣለን፤ |
| · | የጊዜ ሀብታችንን በአግባቡ እንድንጠቀም ይረዳናል፤ |
| · | ለግል፤ ለቤተሰብ፤ ለማህበራዊ ተግባራት፤ ለሀገራዊ አስተዋጽኦዎች እና ለሌሎች ጉዳዮች በቂ ጊዜ እንዲኖረን ይረዳል፤ |

ስለጊዜ አጠቃቀም በዋናነት የምንነጋገርበትና ተግባራዊ ለማድረግ በጊዜ አጠቃቀም ላይ እራሳችንና ልማዶቻችን እየጎሰምን የምንለማመድበት ዋናው ምክንያት ፈጣሪ የሰጠንን በዚህ ምድር በህይወት የመኖር እድል በአግባቡ ለመጠቀምና የተሰጠንን በህወት የመኖር እድል አላማውን በማሳካት ለራሳችን፤ ለማህበረሰባችን እና ለሀገራችን የሚሆነውን ለማከናወን እንድንችል ስለሚረዳን ነው፡፡

በዚህ ምድር የሚኖር ፍጥረት ሁሉ በህይወት ለመኖር የማይጥር የለም:: ከህጻናት ጀምሮ እስከ አረጋውያን ድረስ ለመኖር ሲፍጨረጨሩ ማየት እሙን ነው::ለምሳሌ አንድ ነገር አይናችን ሊነካን ቢፈልግ ሁሉም ለመከላል የቻለውን ሁሉ ያደርጋል፡፡ ትን ብለን ትንታውን ለመቆጣጠር የተቻለንን ሁሉ ለማድረግ እንሞክራለን፡፡ ይህ ድርጊት የሚያሳየው የሰው ልጅ በምድር ላይ ለመኖር የተሰጠውን እድል ለመጠቀም ያለውን ተጋድሎ ነው፡፡

የሰው ልጅ በዚህ ምድር ለመኖር ፈጣሪ የሰጠውን እድል በውጤታማነት ለመጨረስ ስለጊዜ ያለውን አመለካከት በመቀየር የጊዜ አጠቃቀሙንና አያያዙን እለት ከእለት በመፈተሸና በማስተካከል መንቀሳቀስ አለበት::

ሁሉም ነገር ያለጊዜው፤ ያለቦታው ሲገኝና ሁኔታዎች ሲቀያየሩ አስቸጋሪም፤ተቸጋሪም ነው የሚሆነው፡፡ ተመሳሳይ ጊዜ ለዳዊት ድልን ሲያጎናጽፍ፤ ለጎሊያድ ደግሞ ውድቀት ሆኖ በመጽሐፍ ቅዱስ አንብበናል::

የሕይወት ጉዟችን ስኬታማ እንዲሆን ካስፈለገ ጊዜ የህይወት መስመራችን መቋጠሪያ ሰንሰለት የሁለመናችን መስፈሪያ በመሆኑ ውድ፤ እጅግ ጠቃሚና አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡

ይህም ማለት እንዲሁ እየባከኑ ቀንን ከማሳለፍ ለአስፈላጊው ነገር ትክክለኛውን የጊዜ ቀመር በመተመን፤ ውጤታማነታችንን በማየትና በመገምገም የጊዜን አጠቃቀም በሚመለከት የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት ማለት ነው፡፡

## ደቀመዛሙርት

ይህ አምድ በዋነኛነት የተማሪዎች ድምፅ እና ተማሪነትን የሚመለከቱ ፅሁፎች ይቀርብበታል

# በቴክኖሎጂ ዕውቀት የተፍታቱ እጆች የመፍትሄ ምንጮች ናቸው

<u>በሙሉጌታ ዘለቀ</u>

በቴክኖሎጂ መር እድገት ውስጥ ለማደግ ደፋ ቀና የሚሉ አገሮችም ትኩረትና ውሏቸውን በዜጎቻቸው የአእምሮ ውጤት ላይ በማድረግ በሙከራና ስኬት ውስጥ ሆነው እናያቸዋለን:: አገራችን ኢትዮጵያም በዚሁ ጎዳና ካሏት የቴክኖሎጂ ተቋማት ውስጥ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ባሕር ዳር ቴክኖሎጂ ተቋም አንዱ ነው:: ታዲያ በዚህ ተቋም ውስጥ ሆነው ለፈጠራ ሴትተቀን የሚኳትኑ እጆች ተሸልመዋል::



የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዜዳንት ዶ/ር እሰይ ከበደ ለተማሪዎች ሽልማት ሲያበረክቱ

በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚከሰቱ ችግሮች ሀገር በቀል መፍትሄዎችን ለማምጣት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሳይንሳዊ መፍትሄዎችን ከማምጣት አንፃር አውንታዊ ሚና ይጫወታሉ:: በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የባሕር ዳር ቴክኖሎጂ ተቋም የሚገኙ ተማሪዎች ቴክኖሎጂ ተቋሙ ባቋቋመው የቢዝነስ ኢንኩቤሽን እና ቴክኖ ኢንተርፕርነርሺፕ ሴንተር (BiTec) መሰረት በማድረግ የቀሰሙትን እውቀት በመጠቀም ከአኩሪ አተር ተረፈ ምርት ኮላ /ማጣበቂያ / ግሉ በማዘጋጀት ህብረተሰቡን የሚጠቅም የምርምርና የፈጠራ ስራን በመስራት በሀገር ዓቀፍ ደረጃ ተወዳድረው በማሸነፍ ተሸላሚ ሆነዋል::

በተማሪዎች የተሰራው የምርምርና የፈጠራ የዘይት ፋብሪካዎች የሚጠቀሙት የአኩሪ አተር ተረፈ ምርትን ለከብቶች መኖ ከሚሰጠው ጥቅም ውጭ እስካሁን እዚህ ግባ የሚባል አገልግሎት ሳይሰጥ ይባክን እንደነበር የፈጠራ ባለቤት የሆኑ ተማሪዎች ይናገራሉ::

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የባሕር ዳር ቴክኖሎጂ ኢንስትቲዩት የተማሪዎችን የፈጠራ ስራ በመረዳት እና የተለዬ ትኩረት በመስጠት በGiz የፕሮጀክት በመታገዝ ቢዝነስ ኢንኩቤሽን እና ቴክኖ ኢንተርፕርነርሺፕ ሴንተር (BiTec) ቤተሙከራ አደራጅቶ ተመሳሳይ የሆነ የማህበረሰቡን ችግር ፈች የሆኑ ምርምሮች እየተሰሩበት ይገኛል:: የዘይት ፋብሪካዎች የሚጠቀሙትን አኩሪ አተር ጭማቂ (ተረፈ ምርት) ኮላ ማጣበቂያ ግሉ መስራታቸው እና በሀገር አቀፍ ደረጃ ተወዳድረው ትልቅ ስኬት በማስመዝገባቸው የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ባሕር ዳር ቴክኖሎጂ ኢንስትቲዩት የእውቅና እና የእንኳን ደስ ያላችሁ ፕሮግራም በማዘጋጀት የተቋሙ ሳይንቲፊክ ዳይሬክተር ዶ/ር ሰይፉ አድማሱ ጨምሮ የዩኒቨርሲቲው ም/ፕሬዚዳንቶች ተገኝተው ለተሸላሚዎች የእንኳን ደስ ያላችሁ እና የማነቃቃቂያ ንግግር አድርገዋል:: በተለዬ መልኩ የፈጠራ ስራው ለስኬት እንዲበቃ በገንዘብና በማቴሪያል ድጋፍ ያደረገው Giz የፕሮጀክት ለስራ ማስኬጃ ገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ከፍተኛ አስተዋፆ አበርክቷል::

ተማሪዎቹ ስለሰሩት የፈጠራ ስራ ሲያብራሩ የፈጠራ ስራው የመነሻ ሃሳብ ከመመረቂያ ጽሁፍ (Thesis) ሃሳቡ መፍለቁን እና ከቡድናቸው ውስጥ ባሉ ተማሪዎች አማካኝነት የፈጠራ ሀሳቡ መዳበሩን እና ችግር ፈች ለሆነ የፈጠራ ስራ መብቃቱን ተማሪዎቹ ይናገራሉ::

በመሆኑም ሃሳቡን በጥልቀት በማየትና በመመርመር በተሻለ መልኩ የፈጠራ ሀሳብ ተጨምሮበት በማስተካከል እና በማደራጀት ወደ ንግድ ሃሳብ ቀይረው በሀገር አቀፍ ደረጃ ተሸላሚ እንዲሆን እና ለወደፊቱም ወደተግባር ሲገባ የስራ እድል ከመፍጠርም ባለፈ ሀገራችን በኮላ ምርት ራስን ከመቻል አንፃር የላቀ አስተዋፆ ያበረክታል ሲሉ ተናግረዋል::

የማጣበቂያ ግሉ (ኮላ) ለማምረት በዋናነት የተጠቀሙት ጥሬ ዕቃ “Defatted soy flour” (አኩሪ አተረን እንደ ጥሬ ዕቃ የሚጠቀሙ የዘይት ፋብሪካዎችን ተረፈ ምርት) ሲሆን ጥራትና ብቃቱን ገበያ ላይ ካለው ተወዳዳሪ ለማድረግ ሲባል ሌሎች ግብዓቶችን መጠቀማቸውን የቡድኑ አባላት ይናገራሉ::

በተቋም ደረጃ የሚሰሩ በርካታ የምርምር ስራዎች ብዙ ተለፍቶባቸው የህብረተሰቡን ችግር ከመፍታት ይልቅ የሽልፍ ማሞቂያ ሆነው ይቀራሉ:: ሀገራችን ካለባት ተደራራቢ እና አጣዳፊ የህብረተሰብ ችግሮችን ለመቅረፍ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙ መምህራን መሬት የነካ የምርምር ስራሞችን መስራት ይጠበቅባቸዋል::

ተማሪዎቹ ቀንና ሌሊት ጠንክረው በሰሩት የምርምር ስራ ጀርባ ለፈጠራው መሳካት ትልቁን ሚና የተጫወተው እና የሚያስፈልጋቸውን ማንኛውንም እቃዎችን በመግዛት፣ የማማከር ስራን በመስራት የዩኒቨርሲቲው ሚናው የጎላ መሆኑን ይገልፃሉ:: ከዚህ በተጨማሪ ለፈጠራቸው መነሻ የሆነው ጥሬ ዕቃ ሀገር ውስጥ በቀላሉ የሚገኝ በመሆኑ የተማሪዎችን የትኩረት አቅጣጫ መሳቡን ይናገራሉ::

ተማሪዎች በየጊዜው የሚዎስዷቸው ስልጠናዎች የፈጠራ ስራው ገበያ ላይ ካለው የኮላ ምርት ተወዳዳሪ የሆነ ምርት (ናሙና) ይዘው መቅረባቸውን ተማሪዎች ይናገራሉ::

በአሁኑ ሰዓት በተማሪዎች አማካኝነት በመመስረት ላይ ያለው የአኩሪ ኮላ አምራች ካምፓኒ በምርት ሙከራ (ፕሮቶታይፕ) ደረጃ ላይ የሚገኝ ከመቶ በላይ የተለያዩ የሙከራ ደረጃዎችን አልፎ በአሁኑ ሰዓት በከፍተኛ መጠን የደንበኞችን ፍላጎት ሊያሟላ በሚችል መልኩ ገበያ ላይ ካለዉ ምርት ተወዳዳሪ የሆነ ደረጃውን የጠበቀ በቤተ ሙከራ ደረጃ መመረት የሚችል የምርት ሂደት ላይ ነው::

የፈጠራው ባለቤት የሆኑት ተማሪዎች ወደ ቢዝነሱ ዓለም ለመግባት ወይም

ወደ ገፅ 5 ዞሯል

# ጤንነት

## በየሳምንቱ አቮካዶ መመገብ የልብ ሕመም አደጋን ሊቀንስ ይችላል

ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ህክምና ሳይንስ ኮሌጅ የፌስቡክ ገፅ የተወሰደ



በየሳምንቱ አቮካዶ የሚበሉ ሰዎች አቮካዶ እምብዛም ከማይመገቡ ሰዎች ጋር ሲወዳደር ለልብ እና የደም ቧንቧ በሽታ የመጋለጥ እድላቸውን ሊቀንስ ይችላል ሲል በሃርቫርድ ቲ.ኤች የቻን የህብረተሰብ ጤና ትምህርት ቤት (HARVARD T.H Chan School of Public Health) ተመራማሪዎች የተመራው አዲስ ጥናት አመልክቷል።

ተመራማሪዎቹ እንደ ቅቤ፣ አይብ ወይም የተቀነባበረ ስጋን የመሳሰሉ የእንስሳት ተዋፅኦዎችን በተመጣጣኝ መጠን በአቮካዶ መተካት የልብና የደም ሥር (cardiovascular) በሽታዎች የመከሰት እድላቸው ዝቅተኛ መሆኑን አረጋግጠዋል።

ጥናቱ መጋቢት 22፣ 2014 ዓ.ም በጆርናል ኦፍ ዘ አሜሪካን የልብ ማህበር (Journal of the American Heart Association) ላይ ታትሟል።

ተመራማሪዎቹበነርሶችየጤናጥናት እና በጤና ባለሙያዎች ክትትል ጥናት ውስጥ ከ110,000 በላይ ሴት እና ወንድ ተሳታፊዎች የ30 ዓመታት መረጃን ተመልክተዋል። የተለያዩ የልብና የደም ሥር ነክ ጉዳዮችን እና አጠቃላይ የአመጋገብ ስርዓትን ከግምት ውስጥ ካስገቡ በኋላ በጥናቱ ወቅት ቢያንስ በሳምንት ሁለት ጊዜ ግማሽ አቮካዶ የበሉ ሰዎች የልብ በሽታ የመጋለጥ እድላቸው 16 በመቶ ዝቅተኛ እና የልብና የደም ቧንቧ በሽታዎች የመጋለጥ እድላቸዉ 21 በመቶ ዝቅተኛ መሆኑን አረጋግጠዋል።

በጥናቱ ወቅት በቀን ግማሹን የእንስሳት ተዋፅኦ አመጋገባቸዉን በአቮካዶ የተኩ ሰዎች የልብና የደም ቧንቧ በሽታዎች የመጋለጥ እድላቸው ከ16-22 በመቶ ቀንሷል። "እንደ አይብ እና የስጋ ያሉ የተወሰኑ ግባቶችን እና ቅባት የያዙ ምግቦችን በአቮካዶ መተካት ሀኪሞች እና ሌሎች የጤና እንክብካቤ ባለሙያዎች ማለትም የተረጋገጠላቸዉ የስ-ምግብ ባለሙያዎች ከታካሚዎች ጋር ሲገናኙ ሊያደርጉት የሚችሉት ነገር ነው፤በተለይ አቮካዶ ጥሩ በደንብ ተቀባይነት ያለዉ ምግብ ስለሆነ።"

ሲሉ መሪ ደራሲ ሎሬና ፓቼኮ፣ በሃርቫርድ ቻን ትምህርት ቤት የስነ-ምግብ ዲፓርትመንት የድህረዶክትሬት (Postdoctoral) ጥናት ባልደረባ በዜና መግለጫ ላይ ተናግረዋል።

---

Tibebe Ghion Specialized Hospital in Collaboration with a Team of Specialist Doctors from Israel Provide Laparoscopic Surgery Services to patients.

April, 2022





## ኪነጥበብ እና ባህል

# የጉዞ ማስታወሻ

በሽጋዉ መስፍን

መጋቢት 2/2014ዓ.ም ዕለተ አርብ ከጠዋቱ 11፡00 ሰአት ከእንቅልፌ ነቃሁ፡፡

በታሪክ ስትወሳ እንጂ በአይኔ አይቻት ወደማላዉቃትና የወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞን ዋና መቀመጫ ወደሆነችዉ ሁመራ ከተማ ለመስክ ስራ ለመጓዝ ነበር፡፡

ጉዞዉም የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የጤና ስፖርት ልዑክ ቡድን አባላት በሁመራ ከተማ የሚያደርጉትን ጉብኝት ለመዘገብ ታላሚ ያደረገ ነበር፡፡ በጠዋት በመነሳት ወደ ጉዞዉ የመነሻ ቦታ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ህንፃ ፊት ለፊት ደረስኩ፡፡

ከፊት ለፊቴ ሽንጣም አዉቶቡስ ከነግርማ ሞገሱ ቆሞ ይታያል፡፡ የእኛ መጓጓዣ መሆኑ ነዉ፡፡ ጠጋ ብየ እንዴት አደራችሁ? በማለት ወደ ዉስጥ አመራሁ፡፡ መሪዉ ላይ የተቀመጠው ጠይም ቁመተ ሎጋ ጎልማሳ ፈገግ በማለት እግዚአብሔር ይመስገን አለኝ፡፡

ወደኋላ ስመለከት አነስ አነስ ያሉ ሻንጣዎችን የያዙ ወጣቶች አልፎ አልፎ ወንበሮች ላይ ተቀምጠዋል::የተወሰኑትን አዉቃቸዋለሁ፡፡ ሰላም ብያቸዉ እኔም ወንበር ይዤ ቁጭ አልኩ::

በጉዞዉ ተሳታፊ የሆኑ ሰዎችን መጠባበቅ ጀመርን፡፡ ያዉ የሀበሻ ቀጠሮ አይደል በ11፡00 ሰአት ለመገናኘት ብንቀጣጠርም እስከ 12፡30 ሰአት ሁሉም ተጓዥ መሰባሰብ አልቻለም፡፡

አንዳንዱ ለጓደኛዉ ይደዉላል፤ ሌላዉ ትዕግስቱ አልቆ ባክህ እንሂድ ይላል፡፡ ስንወዛገብ 1፡00 ሰአት ሞላ፡፡

ተጓገሮቹ የዩኒቨርሲቲያችን የእግር ኳስና የቮሊቮል የጤና ስፖርት ልዑካን ቡድን አባላት ሲሆኑ የልዑካን ቡድን አባላቱ ሁሉም ወንዶች ናቸዉ፡፡ ብቸኛዋ ሴት ከእኔ ጋር የተመደበችዉ የካሜራ ባለሙያ ነች፡፡ አርፍደዉ ከደወልንላቸዉ አንዱ ስለነበረች በኮንትራት ባጃጅ ከተፍ አለች::የቮሊ ቮል አሰልጣኙ የቤት መኪናቸዉን ይዘዉ ከች አሉ፡፡ አጠር ብለዉ ወፈር ያሉ ከጠይም ፊታቸዉ ላይ ፈገግታ የማይለያቸዉ ሰዉ ናቸዉ፡፡

ከመግባታቸዉ ኳ..ኳስ.. እረሳሁ! አንዴ በመኪና ሂጄ ላምጣዉ? አሉ፡፡ በአዎንታ ተመለከታቸዉ፤ ፈጥነዉ ሁለት ኳሶችን በመያዝ እየከነፉ መጡ፡፡

ጉዞ ተጀመረ፡፡ሰዓቱ 1፡20 ሆኗል::ማልደን የመጣን ሰዎች ብዙ በመቀመጣችን እያጉረመረምን ሌሎቹ እየተሳሳቁ መጓዝ ጀመርን:: ወደኋላ ዘወር ስል መኪናዉ አፍ እስከ ገደፉ ሞልቷል፡፡ የሰዉ ብዛት ልብ ይሞላል፡፡

ጉዞዉን አሀዱ ስንል የተጓገሮቹ ጨዋታ ጀመረ፡፡ ከተጓገሮቹ ብዙዎቹ አፍላ እድሜ ላይ ያሉ ወጣቶች ናቸዉ፡፡ ከስፖርት በተጨማሪ በኮሜዲያን ስራ ቢሰማሩ የሚዋጣላቸዉ ወጣቶች እንዳሉ ከጨዋታቸዉ መረዳት ይቻላል፡፡

ሾፌራችንም ያንን ሽንጣም አዉቶቡስ ያምዘገዝገዉ ጀመር:: ከባሕር ዳር ከተማ ወጥተን ዘንዘልማንና ሀሙሲትን አልፈን ወደ ወረታ ከተማ አመራን፡፡ ሜዳማውን የፎገራ ለምለም ምድር ስናይ ወሩ መጋቢት መሆኑን ረሳነዉ፡፡ በጤፍ፣ በስንዴ፣ በሽንኩርትና ሌሎች አዝዕርቶች የተሞላ የተንጣለለ መሬት ይታያል::

አይንን ከስፍራዉ ለመንቀል ያስቸግራል፡፡ የፎገራ ወረዳ ዋና ከተማ ወረታ፣ አዲስ ዘመን፣ ማክሰኝት...ከተሞችን እያየን ከታሪካዊቷ ጎንደር ከተማ ገባን፡፡

ጎንደር በተራራ የተከበበች፤ በትልልቅ ፎቆች የተሞላችና ወይና ደጋ የአየር ፀባይ ያላት ዉብ ከተማ ነች፡፡ ጎንደር ስንደርስ የከተማዋ ልዩ መገለጫ ከሆነዉ የፋሲል ቤተ መንግስት ጎን ለምሳ ቆምን፡፡ የጎንደር ህዝብ እንግዳ ተቀባይ ለመሆኑ እማኝ መጥቀስ አያሻም፡፡ በየ ሆቴሉና በየካፌዉ ያገኘዉ ሰዉ ሁሉ በፍቅርና በትትህና ያዋሩናል፡፡ለጠየቅናቸዉ ሁሉ ቀና መልስ ይሠጡናል::ምሳ በልተን ጉዞ ጀመርን፡፡

ከጎንደር ተነስተን ቁልቁል ስንደረደር ትንሽ እንደተጓዝን በድንጋይ ተራሮች የተከበበች ትንሽ ከተማ አገኘን፡፡ ትክል ድንጋይ እንደምትባል ነገሩን፡፡

እዉነትም ትክል ድንጋይ! ዙሪያዋ የተተከሉ በሚመስሉ የድንጋይ ተራሮች፣ በድንጋይ ካብ የተሰሩ ጥንታዊ ቤቶች ያሏትና ወይና ደጋ የአየር ንብረት ያላት ከተማ ነች፡፡

ትክል ድንጋይን አልፈን ቁልቁል ስንሸመጥጥ ታች አርማጭሆ (ሳንጃ) ደረስን፡፡ ዙሪያዋ በሳር የተሞሸሩ ሰንሰለታማ ተራሮች ያሉባት አነስተኛ ከተማ ነች::

በየመንገዱ ግራና ቀኝ ስንመለከት በመንጋ የሚንቀሳቀሱ የቀንድ ከብቶች ጉንዳን መስለዉ በመስመር ይጓዛሉ፡፡እንደወላፈን የሚለበልበዉ የፀሀይ ሙቀት በመስኮት ሲገባ የፊትን ወዘና ይለዉጣል፡፡ሙቀቱን እያራገብን፤ ድንቅ ተፈጥሮን እየታዘብን፤ ስንጓዝ ሶሮቃ የተሰኘች በለምለም ዛፎች ያሸበረቀች ሞቃታማ ከተማ አገኘን፡፡ ከተማዋ የዳንሻ መገንጠያ መሆኗን ነገሩን፡፡

እኛም ጉዟችንን ወደ ዳንሻ አደረግን፡፡ዳንሻ ስንደርስ በርካታ የጭነት መኪኖች በየመንገዱ ዳር ቁመዋል፤ በርካታ ወጣቶች በየዛፉ ስር ተኮልኩለዋል፡፡ ዳንሻ በለምለም ዛፎች የተሞላች ዉብ ከተማ ነች፡፡ ዳንሻ ላይ አረፍ ብለን ሻይ ቡና እንድንል የጉዞዉ አስተባባሪዎች ነገሩን፡፡

ወርደን ወደ አንድ መናፈሻ አመራን፡፡ ለሽንት ወደ ዉስጥ ገባሁ፡፡ ቤት ዉስጥ በግምት ከ10–12 ዓመት የሆነ ጠይም መልከ መልካም ህጻን ልጅ ከገመድ ወንበር ላይ ቁጭ ብሏል፡፡ አ...አቡ... ሽንት ቤት የት ነዉ? አልኩት፡፡ አልመለሰልኝም ቀና ብሎ አየኝ:: እኔም አቡሽ ብየ ደፍሬ ልጠራ ያልኩትን አፌን የያዘኝ ጭኑ ላይ ጣል ያደረጋት አንድ እግር ታጣፊ ክላሽን ኮፕ መሳሪያ ነች፡፡ ወይ ክላሽ አያያዝ ህፃን አይመስልም:: አቡሽም ትንሽ ካስተዋለኝ በኋላ

ሽንት ቤቱን በእጁ በመጠቆም አሳየኝ፡፡ደርሸ ተመለስኩ፡፡

ከተማዋን ከጓደኞቼ ጋር ዘወር ዘወር ብለን ለማየት ሞከርን፡፡ “ብ/ጀነራል ሙሉአለም አድማሱ የተከበበበት ቦታ ይህ ነዉ::፡” ሲሉ ቦታዉን ቀድመዉ የሚያዉቁ ሰዎች ሲያወሩ ሰማሁ፡፡

ጆሮዬ ቆመ፤ አይኔ አማተረ፡ አካባቢዉ እንደነገሩ የተሰሩ ቤቶች አሉበት፡፡ዙሪያዉን ትልልቅ ዛፎች ይታያሉ፡፡ በዚያ በረሃ የጥይት ሀሩር ታክሎበት ምን ያህል ከባድ እንደሚሆን ሳስበዉ የእዉነት ጨነቀኝ፡፡

ያዉም ሶስትና አራት ቀን ሙሉ ያለ እህልና ዉሀ መዋጋት! ሰዉ ቁርጠኛ ከሆነ ምንም ማድረግ ይችላል አልኩ ለራሴ፡፡ ትንሽ ተዘዋዉረን ሻይ ቡና ብለን ወደ አዉቶቡሳችንገብተንጉዞጀመርን፡፡

በአማራ ክልል ወልቃይት ጠገዴ ዞን የበአከር ከተማ አስተዳደር የሚል ታፔላ አነበብኩ፡፡ በአከር ትንሽ ከተማ ነች፡፡

ከተማዋን እንዳለፍን እንደመቀነት የተጠመጠሙ የድንጋይ ምሽጎችን ተመለከትን፡፡ በአካባቢዉ የበረሃዉ ሀሩር ያልበገራቸዉ የመከላከያ ሰራዊት አባላት መስመር ሰርተዉ ሲንጎማለሉ ስታይ ይበልጥ ደህንነት ይሰማሀል፡፡

ከቀደመዉየአገዛዝስርዓትበትክክል ነፃ የወጣ ህዝብ ያለዉ ወልቃይት ጠገዴ ዞን መሆኑን ለማረጋገጥ እማኝ አያሻም፡፡ የኢትዮጵያ ልዩ ምልክት የሆነዉ ልሙጥ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ሰንደቅ

አላማ በየከተሞቹ መሀል በረጃጅም ፖሎች ላይ በግርማ ሞገስ ተሰቅሎ ሲዉለበለብ ማስተዋል በቂ ነዉ፡፡

ዙሪያ ገባዉን በአይናችን እየቃኘን፤ ድንቅ ተፈጥሮን እየታዘብን ወደ ዞኑ መቀመጫ ሁመራ ከተማ ተቃረብን፡፡

ፍም የመሰለችዉ ፀሀይ ወደ ማደሪያዋ ለመግባት ተቃርባለች::እኛም በቅርብ ርቀት ዉብ ከተማ ማስተዋል ጀመርን፡፡ የመንገዱ ስፋትና ጥራት፣ የዛፎቹ ልምላሜ፣ ከምሽቱ ነፋሻማ አየር ጋር ተዳምሮ ቀልብን ይስባል::

በደንብ ማስተዋል ጀመርኩ:: ሾፌራችንም ያንን ሽንጣም አዉቶቡስ በተንጣለለዉ አስፋልት እንደልቡ ያሽከረክረው ጀመር:: አንድ ትልቅ አደባባይ አገኘን፡፡

በዙሪያዉ አራት ያህል መንገዶች አሉ፡፡ አንደኛዉን ተከትሎ ከነፈ፡፡ ተጓዦችም አልጋ ወዳለበት ቦታ ዉሰደን አልነዉ፡፡

የአካባቢዉ ወጣቶች ወደ መኪናችን ትኩር ብለዉ ይመለከታሉ፡፡ ሾፌራችን በመስኮት ብቅ በማለት አልጋ ያለበትን ቦታ ጠየቃቸዉ::

አንደኛው ልጅ ስማርት ሳይክል በመያዝ ተከተሉኝ አለን:: ተከትለነዉ ወደ አንድ ሆቴል አመራን፡፡ አልጋ ስንጠይቅ የለም ተባልን፡፡አሁንም እንድንከተለዉ ነገረን፤ ተከተልነዉ፡፡ሌላ ቦታ ስንሄድ አልጋ እንዳለ ነገሩን፡፡ ውሃ፣ መብራት…አለዉ? ጠየቅን::

ውሃ አለ፤ መብራት ጀኔሬተር ስላለ ይኖራል አሉን፡፡ ለካስ ከተማዋ መብራት የላትም፡፡ ሁላችንም ወረድን፡፡ የአልጋ ቤቱ እንግዳ ተቀባዮች ምን አይነት አልጋ ይሁንላችሁ? ሲንግል ወይስ ዳብል? ከዉስጥ ወይስ ከዉጭ? ይሉን ጀመር፡፡

አንዱ ጓደኛችን ገረመዉና “ደሞ ከዉጭ አልጋ አለ እንዴ?” ብሎ ጠየቀ፡፡አስተናጋጁ ሳቅ ብሎ አዎ አለ፤ በረንዳ ላይ ፍራሽ አንጥፎ መተኛት ይቻላል፡፡እንዳዉም ለሙቀቱ ተመራጭ ነዉ አለን፤ ተሳሳቅን፡፡በማናዉቀዉ ከተማ፣ ያዉም በጦርነት ቀጠና ከዉጭ ስንተኛ አስባችሁታል? ሁላችንም ከዉስጥ ስጠን ብለን፤ በግልም በጋራም አልጋ ያዝን:: ትንሽ በአካባቢዉ ዘወር ዘወር ካልን በኋላ እራት መብላት ስለነበረብን ግማሻችን ከያዝነዉ ሆቴል ሌሎቻችን ደግሞ ከሆቴሉ ፊት ለፊት ካለች አነስተኛ ምግብ ቤት ታደምን፡፡ ምን ልታዘዝ? አሉን አስተናጋጆች፡፡ ቤት ያፈራዉን ጠይቀን የተለመዱ ምግቦችን አዘዝን፡፡ ሽሮ፣ ምስር፣ አትክልት ብለን በጋራ ተቀምጠን መጠባበቅ ጀመርን፡፡

ምግቡም በትሪ መጣ፡፡ ተከታትሎ ወጥ በትንሽ ድስት የያዘ ህፃን ልጅ መጣ፡፡ድስቷ በጣም ትንሽ ነች፡፡ ወጡን ከእንጀራዉ ላያ ሲያደርገዉ ጠብ ብላ ቀረች፡፡ ተሳሳቅን፤ ህፃኑም አስቂኝ ነገር ነዉ፡፡ ምን ሆናችሁ? አለን፡፡ ከመካከላችን አንዱ ወጡ ይኸዉ ነዉ? አለዉ፡፡ህፃኑም ድስቷን ወደ ሰዉዬዉ ጠጋ አድርጎ ጥረገዉ! ሲለዉ እኛ የበለጠ ሳቅን፡፡ ልጁ ግን ከልቡ ስለነበር መሳቃችን አስገረመዉ፡፡

በዚህ ሁኔታ ምግባችንን እንደነገሩ በልተን ወደ ሆቴላችን አመራን፡፡ ከሆቴሉ እራት የበሉት ጓደኞቻችን በየጠረጴዛዉ ክብ ክብ በመስራት ቢራ ጠርሙሶች ከጠረጴዛዉ ላይ ደርድረዉ እየተሳሳቁ ይጠጣሉ:: እኛም ሰብሰብ ብለን አንድ ሰፊ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀመጥን:: እንደዬ ፍላጎታችን አዘዝን፡፡ ትንሽ እንደተጎነጨን አንደኛዉ ጓደኛችን ሶሪ! ስልኬን ጣልኩት አለ፡፡ሌላኛዉ ኦ… ቅድም እራት ስንበላ ይዘኸዉ ነበር በማለት የት ሊወድቅ እንደሚችል ፍንጭ ሰጠ፡፡

እኛም ተደናግጠን ወደ ቦታዉ አመራን፡፡የጠፋዉ ስልክ በጣም ዘመናዊ ቀፎ (ስማርት ፎን) ነበር፡፡ሄደን ስንጠይቃቸዉ አንደኛዋ ልጅ ስልክ እንዳላየች ሆኖም ከእኛ ዉጭ ማንም ሰዉ ስላልመጣ እንደማይጠፋ ነገረችን::

አቡሽ አንስቶ ይሆን? አልን አቡሽ ለምግብ ቤቱ እንጀራ ሊያመጣ እንደሄደ ነገረችን፡፡እሱን በመጠባበቅ ላይ እያለን ሌላኛዋ የምግብ ቤቱ ሰራተኛ መጣች:: ምን እንደሆንን ጠየቀችን፤ ነገርናት፡፡ወደ ሆቴሉ እንድንሄድ ነገረችን፤ሄድን፡፡ለካስ የጣልነዉ እኛ መሆናችንን ስለተረዳች ለሆቴሉ እንግዳ ተቀባዮች ወስዳ ሰጥታቸዋለች፡፡ወይ ጉድ! አልኩ በልቤ ስንት ኪስ አዉላቂ ባለበት ሀገር ይህንን የመሰለ ስልክ ወድቆ ሲገኝ አንስቶ የሚሰጥ ሰዉ አለ? ታማኝታቸዉ አስቀናኝ፡፡

ተመልሰን ወደ ሆቴሉ ስንሄድ ጨዋታዉ ደርቷል፡፡ጠረጴዛዎቹ በቢራ ጠርሙስ ተጨናንቀዋል፡፡ የጎንደር ሙዚቃ በትልቅ ድምፅ ማጉያ(ሞንታርቦ) ያስገመግማል::

ቁጭ አልን፤ ቀመስን፤ ተጎነጨን፤ ጠጣን፤ ሞቅ አለን፡፡

አንድ ሁለት ሲሉ የነበሩ ወጣቶች ሙዚቃዉ ሸነጣቸዉ፤ ተነሱ፤ ዳንስ ተጀመረ፡፡የዳንስ አይነት አየን፡፡ቆሞ ከሚወዛወዝ እኔን መሰል እንደእንዝርት የሚሾር ዳንሰኛ ተመለከትን፡፡የሆቴሉ አስተናጋጆች ፈዘዉ መመልከት ጀመሩ፡፡ጆሯቸዉን ቢቆርጧቸዉ አይሰሙም፤ በጣም ተገርመዋል፤ ሰዉ እንደራባቸዉ ያስታዉቃሉ፡፡

ምሽቱን በጥሩ ሁኔታ ገፋነዉ

5፡00 ሰዓት ገደማ ወደ መኝታ ክፍላችን አመራን፡፡ክፍሉ በጣም ይሞቃል፡፡ወደ መታጠቢያ ክፍሉ ገባሁ፤ ዉሃዉ ሲወርድ ፊትን ያቃጥላል፡፡መስኮቶችን ከፍተን ተኛሁ፡፡ ስለደከመኝ ትንሽ እንቅልፍ ወሰደኝ፡፡8፡00 ሰዓት ሲሆን ከእንቅልፌ ነቃሁ::

እጄን ወደ አንገቴ ስሰድ ባልዲ ዉሃ የተደፋብኝ መሰለኝ፡ በጣም አልቦኛል፡፡ትንሽ ስገላበጥ ቆይቼ በጣም ደስ የሚል ቀዝቃዛ ሻወር ወሰድኩ፡፡ከማታዉ ዉሃ እጅግ በተቃራኒዉ ነበር ቅዝቃዜዉ፡፡ በድጋሚ ትንሽ አረፍ አልኩ፡፡

ወዲያዉኑ የሰዎች ድምፅ ሰማሁ፤ ተነሱ ረፍዷል ይላል አንደኛዉ.ተነስቼ ወጣሁ፤አብዛኞቹ ልጆች ተነስተዉ በረንዳ ላይ ቁመዋል፤ ከፊት ለፊታችን አልጋ የያዙት ጓደኞቻችን በረንዳ ላይ ተኝተዉ አየን፡፡

ምን ሆናችሁ ስንላቸዉ ሙቀቱ አላስተኛን ሲል ፍራሽ አዉጥተን ተኛን አሉን፡፡ለካስ ወደዉ አልነበረም አስተናጋጆቹ ከዉስጥ ወይም ከዉጭ ያሉን ፡፡ ሁላችንም ተሰባስበን ወደ ተከዜ ድልድይ ለመሄድ መኪና ዉስጥ ገባን፡፡አልፎ አልፎ የከተማዋ ነዋሪዎች በእግራቸዉ ይንቀሳቀሳሉ፡፡በአህዮች የሚጎተቱ ጋሪዎችን የያዙ ወጣቶች በፍጥነት ይከንፋሉ፡፡የመንገዱን አቅጣጫ ጠይቀን ወደ ተከዜ ወንዝ ሄድን ፡፡

በጣም ቅርብ ነዉ፡፡ተከዜ የሁመራ ከተማ አዋሳኝ የኢትዮ አርትራና ኢትዮ ሱዳን ድንበር ነዉ፡፡ወደ ወንዙ ለመግባት በወንዙ ዳርቻ ያለዉ የአሸዋ ቁልል ለሸፍን ጫማ ብዙም አልተመቸንም፤ አንዳንዶቻችን ጫማ አወለቅን፤ ሌሎቻችን እንደምንም ተንቆራጠን ከዉሀዉ ደረስን፡፡

በርካታ ወጣቶች ይዋኛሉ፡፡እኛም ልብሳችንን አዉልቀን ዘዉ ብለን ገባን፡፡ወዘ ልውጥ በመሆናችን የወጣቶቹን ትኩረት ስበናል፡፡እንደልባችን ተንቦጫረቅን! ዉይ ዉሃዉ ደስ ሲል! ጥርት ያለ፤ በጣም ሰፊና በፍጥነት የሚሄድ ወንዝ፡፡ዉጡ ዉጡ አይልም ፡፡ከ1 ሰዓት በላይ እንደልባችን ተዝናንተን ወጣን፡፡

ዳር ለዳር ያሉት ልዩ ልዩ ቀለማት ያላቸዉ ድንጋዮች ልጅነቴን አስታወሱኝ፡፡ከየአይነቱ ለቃቅሜ ያዝኩ፡፡በጣም የሚያምር ቀለምና ልዩ ልስላሴ አላቸዉ፡፡

በመቀጠል የኢትዮ- ኤርትራ መተላለፊያ የሆነዉ ተከዜ ድልድይ ወዳለበት ቦታ አመራን፡፡ወደ ድልድዩ ለመግባት ስንሞክር ማለፍ እንደማይቻል ነገሩን፡፡ የመጣንበትን ስንነግራቸዉ በልዩ ትዕዛዝ እንድንሻገር ፈቀዱልን፡፡የኤርትራ ወታደሮች ከድልድዩ ማዶ መሳሪያቸዉን በተጠንቀቅ ይዘዉ በትኩረት ይከታተላሉ፡፡ ከወዲህ የኢትዮጲያ ባንዲራ ከማዶ ደግሞ የኤርትራ ባንዲራ ፊት ለፊት ይዉለበለባሉ፡፡ የሁለቱን ሀገሮች ሰነንደቅ ዓላማዎች አንጋጠን እያየን ፎቶ ተነሳን፡፡

ተመልሰን በቀጥታ ወደ ሁመራ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ቢሮ አመራን፡፡ስንደርስ ከንቲባዉ አሁን ወጣ አሉን ፡፡ከቦታዉ

ወደ ገፅ 14 ዞሯል

# የሳይንስ ጥግ

ይህ አምድ ሳይንስ እና ቴክኖሎጅ ነክ የሆኑ ፅሁፎች ይቀርብበታል

# What is Cyber Security? Definition, Best Practices & More

By Esubalew Alemneh(PhD)

(Director of ICT 4D Research Center)

## A Definition of Cyber Security

Cyber security refers to the body of technologies, processes, and practices designed to protect networks, devices, programs, and data from attack, damage, or unauthorized access. Cyber security may also be referred to as information technology security. It aims to reduce the risk of cyber-attacks and protect against the unauthorized exploitation of systems, networks and technologies.

## The Importance of Cyber Security

Cyber security is important because government, military, corporate, financial, and medical organizations collect, process, and store unprecedented amounts of data on computers and other devices. A significant portion of that data can be sensitive information, whether that be intellectual property, financial data, personal information, or other types of data for which unauthorized access or exposure could have negative consequences. Organizations transmit sensitive data across networks and to other devices in the course of doing businesses, and cyber security describes the discipline dedicated to protecting that information and the systems used to process or store it. As the volume and sophistication of cyber-attacks grow, companies and organizations, especially those that are tasked with safeguarding information relating to national security, health, or financial records, need to take steps to protect their sensitive business and personnel information. As early as March 2013, top intelligence officials cautioned that cyber-attacks and digital spying are the top threat to national security, eclipsing even terrorism.

## Challenges of Cyber Security

For an effective cyber security, an organization needs to coordinate its efforts throughout its entire information system. Elements of cyber encompass all of the following:

- Network security: The process of protecting the network from unwanted users, attacks and intrusions.
- Application security: Apps require constant updates and testing to ensure these programs are secure from attacks.
- Endpoint security: Remote access is a necessary part of business, but can also be a weak point for data. Endpoint security is the process of protecting remote access to a company's network.
- Data security: Inside of networks and applications is data. Protecting company and customer information is a separate layer of security.
- Identity management: Essentially, this is a process of understanding the access every individual has in an organization.
- Database and infrastructure security: Everything in a network involves databases and physical equipment. Protecting these devices is equally important.
- Cloud security: Many files are in digital environments or "the cloud". Protecting data in a 100% online environment presents a large amount of challenges.
- Mobile security: Cell phones and tablets involve virtually every type of security challenge in and of themselves.
- Disaster recovery/business continuity planning: In the event of a breach, natural disaster or other event data must be protected and business must go on. For this, you'll need a plan. End-user education: Users may be employees accessing the network or customers logging on to a company app. Educating good habits (password changes, 2-factor authentication, etc.) is an important part of cybersecurity.

The most difficult challenge in cyber security is the ever-evolving nature of security risks themselves. Traditionally, organizations and the government have focused most of their cyber security resources on perimeter security to protect only their most crucial system components and defend against known treats. Today, this approach is insufficient, as the threats advance and change more quickly than organizations can keep up with. As a result, advisory organizations promote more proactive and adaptive approaches to cyber security. Similarly, the USA's National Institute of Standards and Technology (NIST) issued guidelines in its risk assessment framework that recommend a shift toward continuous monitoring and real-time assessments, a data-focused approach to security as opposed to the traditional perimeter-based model.

## Managing Cyber Security

A top-down approach to cyber security in which corporate management leads the charge in prioritizing cyber security management across all business practices is usually recommended by cyber security experts and organizations. Companies must be prepared to "respond to the inevitable cyber incident, restore normal operations, and ensure that company assets and the company's reputation are protected." The USA's National

Cyber Security Alliance (NCSA) guideline shows that for conducting cyber risk assessments we have to focus on three key areas: identifying your organization's "crown jewels," or your most valuable information requiring protection; identifying the threats and risks facing that information; and outlining the damage your organization would incur should that data be lost or wrongfully exposed. Cyber risk assessments should also consider any regulations that impact the way your company collects, stores, and secures data. Following a cyber risk assessment, develop and implement a plan to mitigate cyber risk, protect the "crown jewels" outlined in your assessment, and effectively detect and respond to security incidents. This plan should encompass both the processes and technologies required to build a mature cyber security program. An ever-evolving field, cyber security best practices must evolve to accommodate the increasingly sophisticated attacks carried out by attackers. Combining sound cyber security measures with an educated and security-minded employee base provides the best defense against cyber criminals attempting to gain access to your company's sensitive data. While it may seem like a daunting task, start small and focus on your most sensitive data, scaling your efforts as your cyber program matures.

Source: https://digitalguardian.com

# ስብጥር

ይህ አምድ በሌሎች አምዶች ያልተስተናገዱ ልዩ ልዩ ፅሁፎች ይቀርብበታል

## የጉዞ ማስታወሻ ከገፅ 12 የቀጠለ

ስንደርስ ጥበቃዎችን አስፈቅደን ወደ ግቢ ገባን:: ከንቲባዉ ጠይም ዘለግ ያለ ደስ የሚል ፈገግታ ያለዉ ገራገር ዓይነት ሰዉ ነዉ:: ለመግባባት ጊዜ አልፈጀብንም:: የመጣንበትን ጉዳይ ስንነግረነዉ ወደ ቢሮዉ እንዲንገባ ጋበዘን፤ ገባን፤ ብዙ ተወያየን:: በአካባቢዉ ያለዉን ፀጋ፣ ያጋጠማቸዉን ችግርና መፍትሄ ያሉትን ሁሉ ነግረዉን፤ እኛም አስተያየታችንን ሰጥተን ተሰነባበትን::

ከረፋዱ 5:20 ሆነ::ሾፌራችን አዉቶቡሱን ወደ አንድ ነዳጅ ማደያ ነዳዉ::ነዳጅ ሞልቶ ጉዞ ተጀመረ::ከከተማዋ እንደወጣን ጎዕዝ መልካም የሚል ጽሁፍ ታፔላ አየሁ፤በደንብ አላነበብኩትም:: መልካም ጉዞ መሆኑ ነዉ አልኩ:: ነፋሻዉን አየር እየኮመኮምን፤ በደረቅ ጫካ የተሞላ ሰፋፊ መሬት ግራ ቀኝ እየታዘብን፡ ስንከንፍ በድንጋይ የተኮለኮሉና የተቆፈሩ ምሽጎችን አልፈን በአከር ገባን::

ጉዞ ወደፊት! ዳንሻ ስንደርስ ለምሳ ወረድን:: ሰዓቱ 7:00 ሰዓት ሆኗል:: ከካሜራ ባለሙያዋና ከአንድ ሌላ ጓደኞችን ጋር ሆነን ወደ አንዲት አነስተኛ ካፌ ገብተን ምግብ መኖሩን ጠየቅን፤ አለ አሉን:: ምን ምን ምግብ እንዳለ ጠየቅን:: ሽሮ፣ በየአይነት፣ ጊርጊር...አለች አስተናጋጇ::አይነት አምጭልን አልናት::ስታመጣዉ ብዙም አላስደሰተንም::ለርሀባችን ማስታገሻ ብቻ ትንሽ ቀማምሰን አስተናጋጇን ጠራናት::

ስትመጣ ሌላስ ምን ምግብ አለ? አልናት:: ጊርጊር አለችን በፊት ቃሉን ስትነግረን ደግመን መጥራት አልቻልንም ነበር::

ስትደግመዉ ጊርጊር ምንድን ነዉ? አልናት::ቲማቲም፣ ቃሪያ፣ ጊርጊር በአንድ ላይ ሆኖ አለችን::የምታወራዉ ትግርኛ ስለነበር በደንብ መስማት አልቻልንም:: አትክልት ነገር ነዉ? አልናት::አዎ አለች:: አዘዝናት፡ ጊርጊር በእንጀራ መጣ:: አይ ጊርጊር! ሶስታችንም ተያየን፡ ማን መብላት ይጀምር::ጊርጊር ቆስጣ መሰል ስስ ቅጠል ያለዉ አትክልት ነዉ:: አይተነዉ አናዉቅም::ጓደኞችን አንዷን ቅጠል አንስቶ ቀመሰ::እኔም ተከትየ አንዷን ቅጠል ወደ አፌ አልኳት:: ወዲያዉኑ ሳላምጠዉ አፌ እሬት ሆነ፤ ተነስቸ ለመሄድ ጊዜ አልሰጠኝም::እዛዉ ላይ ተፋሁት::ከካፌዉ ያሉት ሰዎች እኛን በመገረም እያዩ ሳቁ:: እኔም በእጅ ስልኬ የጊርጊርን ፎቶ አንስቼ ወደ መኪናችን ሄድን::

ሁሉም ሰዉ ተሰባስቦ ጉዞዉ ቀጠለ::በቡድን በቡድን ጨዋታችንን እያቀለጥን ስንጓዝ በግራ ቀኝ ስርቅ አድርጌ አያለሁ::ከብቱ፣ ፍየሉ፣ በጉ ሜዳዉን ሞልቶት ሳይ አስቀናኝ::ኢትዮጵያ ከአፍሪካ በቀንድ ከብቶች ብዛት አንደኛ ነች:: የሚለዉ የጂኦግራፊ ትምህርት ትዝ አለኝ::

ሳናስበዉ ሳንጃ ከተማ ደረስን፡ ሳንጃ በበርካታ ህዝብና መኪኖች ተጨናንቃለች::

ከከተማዋ ስንወጣ የጉምሩክ ኬላ አገኘን፡የመከላከያ ሰራዊት አባላት፣ የፌደራል ፖሊስና የጉምሩክ ጣቢያ ተቆጣጣሪዎች መኪናችንን አስቆሙት:: አንዲት ቢጫ ጋዎን የደረበች መልከ መልካም፣ ቀይ፣ ቁመተ መለሎ ወጣት ወደ መኪናችን ገባች:: ከኋላዋ አንድ ጥቁር ወጠምሻ የመከላከያ ሰራዊት አባል በቅርብ እርቀት ይከታተላታል::ከመኪናችን ገብታ ፊታችንን ስታየዉ የድካም ስሜት ይታይበታል:: ብዙ ማጨናነቅ አልፈለገችም::

ከፊት ያሉ ሻንጣዎችን ፈተሽ ፈተሽ አድርጋ፤የወንበሮቹን ስር ቃኘት ካደረገች በኋላ የመጣንበትን ጠየቀች::ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ መሆኑን ስንነግራት መልካም ጉዞ በማለት በፈገግታ ሸኘችን::

ትክል ድንጋይ ስንደርስ ከየት መጣ ያልተባለ ዝናብ ያወርደዉ ጀመር::ጉዞዉ ቀጠለ፤ ዝናቡም ወደ በረዶ ተቀየረ::ከየተራራዉ የሚወርደዉን ጎርፍ ሳይ ሁመራ ትዉስ አለኝ::ወይ ተፈጥሮ! አንዱ ሐሩር ሙቀት ሌላዉ በበረዶ የተሞላ ጮቄ አይገርምም አልኩ ለራሴ::

ከቀኑ 12:30 ጎንደር ከተማ ደረስን:: አዉቶቡሳችንን ወደ ማሳደሪያ ወስደን ወደ ሆቴል አመራን::አልጋ አፈላልገን ያዝን:: ትንሽ አረፍ እንዳልን ወጥተን እራት በላን::ምሽቱን እንዴት ማሳለፍ እንዳለብን መወያየት ጀመርን::ኳስ አናይም? አልኩ የእንግሊዝ ፕሪሜርሊግ ተጠባቂ ጨዋታ ስለነበር::

የባህል ምሽት ቤት እንግባ አለ አንደኛዉ::ሌላኛዉም በሀሳቡ ተስማማ:: እኔም ሁለት ለአንድ ስሸነፍ ሀሳቡን ተቀበልኩ::ወደ አንድ ትልቅ የባህል ምሽት ቤት አመራን::

"እንዬ ታከለ ባህላዊ ምሽት ቤት"ይላል::ታዋቂ ቤት መሆኑን ከዚህ በፊት የሚያዉቁ ልጆች ነገሩን::ወደዚያዉ ተያይዘን ሄድን ቀድመዉ የተሰየሙ ጓደኞቻችንን አገኘን::ቤተኛነት ተሰማን::ምን ልታዘዝ አሉን በባህል አልባሳት ያሸበረቁ አስተናጋጆች::

ዳሽን ቢራ አልን በአንድ ድምፅ፡ ጎንደር የዳሽን ቢራ ማምረቻ ፋብሪካ እንዳለ ሁላችንም መረጃዉ አለን::መጣልን!ችርስ በማለት ተያያዝነዉ::አንድ ሁለት ስንል ጨዋታዉ እየደራ መጣ::በቡድን በቡድን በመሆን የሚወዛወዙ፤ ከመድረኩ እየወጡ ከዘፋኞቹ ጋር የሚደንሱ፤ አፍ ላፍ የሚያወሩ ሰዎችን አስተዋልኩ::የቤቱ መብራት በቴክኒክ ችግር ከማስቸገሩ ዉጭ ሁሉም ነገር ደስ ይላል::

የዘፋኞቹ ችሎታና የተወዛዋዦቹ ዲስፕሊን በጣም ይደንቃል:: ባህላዊና ዘመናዊ ሙዚቃዎች በአይነትቀረቡ::የብሔርብሔረሰብ ዘፈኖች እንደጉድ ተቀነቀኑ::ምን አለፋችሁ የእንዬ ቤት መንፈስን ያድሳል፤ የደከመን ያጠነክራል::

ዘፋኞቹ ከመድረክ ወርደዉ ሙዚቃዉ ለደቂቃዎች ፀጥ አለ::ትንፋሽ ለመዉሰድ ይሆናል ብለን በትዕግስት ጠበቅን:: አራት ያህል የቤቱ ተወዛዋዦች በሚያምር ባህላዊ ቀሚስ ተዉበዉና የሚንቀለቀሉ ችቦዎችን ይዘዉ ወደ ዉስጥ ዘለቁ::

መድረክ መሪዉ መድረክ ላይ ወጥቶ ማይክ ጨበጠ፤ ንግግሩን ቀጠለ፤ ጆሮ ሰጠነዉ::ዛሬ ልዩ እንግዶች ስላሉን እንኳን ደህና መጣችሁ ማለት እንፈልጋለን አለ::ዘወር ዘወር ብለን ተያየን:: በብዛት የእኛ ቡድን አባላት ወንበሮችን ቢሞሏቸዉም ሌሎች ሰዎችም በጥንድና በቡድን ተቀምጠዉ ይዝናናሉ::

መድረክ መሪዉ ቀጠለ ዛሬ ልዩ እንግዶች አሉን፤ እነሱም "ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የመጡ የጤና ስፖርት ልዑክ ቡድን አባላት ናቸዉ::" ሲል አዳራሹ በጭብጨባ ቀለጠ::እኛም ኩራት ተሰማን::

እግዜር ይስጣቸዉ የሰዉ ልጅ ሁሌም ሰዉን ቢያከብር እንዴት ደስ ይላል? አልኩ በልቤዉስጤን ደስታ እየናጠዉ::

ከምሽቱ 5፡30 ሰዓት ገደማ ወደ ሆቴላችን አመራን::ጥሩ እንቅልፍ አሳልፈን በጠዋቱ ወደ አፄ ፋሲል ቤተ-መንግስት ሄድን:: በቡድን ስለነበርን አስጎብኚ ተመድቦልን የእያንዳንዱን ህንፃ ምንነትና በማን ዘመነ መንግስት እንደተሰራ ተረከልን::በጣም ደስ ተሰኘን::የማስታዎሻ ፎቶዎችን በግልም በቡድንም ተነሳን::

ከረፋዱ 5፡00 ሰዓት ሲሆን ወደ መኪናዉ ተሰባስበን ጉዞ ወደ ዉቢቷ ባሕር ዳር ሆነ::በሳቅና ጨዋታ ታጅበን የልብ የልባችን እያወራን ወረታ ከተማ ደረስን::

ምሳ በልተን ትንሽ ዘወር ዘወር በማለት ከተማዋን ቃኘናት::ወረታ በጣም የምታምርና ለምለም ከተማ ነች::ሩዝና አጃ ሸማምተን ከያዝን በኋላ ጉዞ ወደ ባሕር ዳር ቀጠለ::ከቀኑ 10:00 ሰዓት ባሕር ዳር ደረስን::

ስፖርት ለጤንነት! ስፖርት ለወዳጅነት! ሁሉም ሰዉ ወደ ቤቱ ተመለሰ::


አበቃሁ!

# እንግዳ

ይህ አምድ የዩኒቨርስቲው ሰራተኞች፣ ተማሪዎች ወይም ሌሎች ታዋቂ እና ተፅኖ ፈጣሪ ሰዎች በዕንግድነት ይቀርቡበታል

በወንዳለ ድረስ

## “ካንች የሚጠበቀውን ማድረግ ከቻልሽ ስኬትን ታገኛለሽ”



ራሄል ድርብ ወርቅ ከህክምና ሳይንስ ኮሌጅ 3.99 በማምጣት የሜዳልያ ተሸላሚ

በሰሜን ሸዋ ዞን ሞረትና ጅሩ ወረዳ የተወለደችው ራሄል ድርብወርቅ ዋለ በሚድዋይፈሪ የትምህርት መስክ 3.99 በማምጣት የመዳልያ ተሸላሚ ሁናለች።

ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል በሞረትና ጅሩ ወረዳ እናውሪት አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የተማረችው ራሄል ከአምስተኛ ክፍል በኃላ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ከአክስቷ ጋር በመሆን ዩኒቨርስቲ እስከ ገባችበት ድረስ ቆይታለች።

ራሄል ዩኒቨርስቲ እንደገባች ልቧ የፈቀደውን ዶክተር የመሆን ህልሟን መማር ባትችልም ዲፓርትመንቱ በመረጣት ሚድዋይፈር መማር የጀመረች ሲሆን በወቅቱ ልቧ የፈቀደውን የትምህርት ክፍል መምረጥ አለመቻሏ ቢረብሻትም፤ ብልህ ልጅ እየበላ ያለቅሳል እንዲሉ መምረጥ በቻለችው የትምህርት ዘርፍ ውጤታማ ለመሆን ወሰነች።

እንደአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ወላጅ ቤተሰቦቸም ዶክተር እንድሆን ይፈልጉ ነበር ትላለች ራሄል የነሱን ፈቃድ ባለመሙላቴም ቅር ብሎኛል ትላለች። በደረሳት ትምህርት ውጤታማ ለመሆን ከታች ክፍል ጀምሮ የደረጃ ተማሪ መሆኗ እና የቤተሰቦቿ የዕለት ዕለት ክትትል እና ድጋፍ በተለይም አዲስ አበባ ያለችው አክስቷ በጥናት ጊዜ ስራ እንዳትሰራ ከምታደርገው በተጨማሪ ‹‹ያለሽን አቅም ከተጠቀምሽ አንች አሸናፊ ነሽ›› እያለች ታበረታታት እንደነበር ባለታሪኳ ትናገራለች።

ራሄል የዩኒቨርስቲ ቆይታዋን ወደ ኃላ ተጉዛ ስታወሳ “የመጀመሪያ ዓመት ላይ ለአካባቢው አዲስ መሆኔ፣ ያልመረጥኩት ትምህርትን ለመማር መግባቴ፣ ቤተሰብ ከሚጠብቀኝ በታች ነው የገባሁት ብየ ማሰቤ ጫናው ከፍተኛ ቢሆንም ትምህርቴን ከማጥናት እና ከመከታተል አልተቆጠብኩም ነበር ትላለች።

”ምክንያቱም አሁን በያዝኩት ትምህርት ውጤታማ ከሆንኩኝ ወደ ምመኘው ግብ መድረስ እችላለሁ ብየ አሰብኩ፤ ሌላው ወደ ዩኒቨርስቲ ስገባ የተከፋትን ቤተሰቦቸን ጥሩ ውጤት በማምጣት ማስደሰት አለብኝ የሚል ግብ ስለነበረኝ ግቢ ውስጥ ያለው መዝናናት እና ሌሎች ነገሮች ሳይበግሩኝ ግቤን ማሳካት ችያለሁ ትላለች።

ባለታሪኳ ለዚህ ውጤት መሳካት የምትከተለውን የአጠናን ዘዴ ስትገልፅ ዩኒቨርስቲ ስገባ ቀደም ሲል የነበረኝ ልምድ መጠቀም መቻሌ እና አዕምሮየ መሸከም እስከሚችል እንጂ እስከሚሰለቸኝ አላጠናም ነበር። ከዚህም በተጨማሪ ትንሽም ጊዜ ሳገኝ ውጤማ በሆነ መልኩ መጠቀም፤ ሳነብም ያለውን መቀበል ሳይሆን ይህ ለምን ሆነ የሚለውን በመጠየቅ እመረምራለሁ።

በዩኒቨርሲቲ ቆይታየ ውጤታማ ለመሆን የትምህርት ክፍለ ጊዜዎቹን በአግባቡ በመከታተል መምህራኖች የሚሰጡትን ሞጅሎች በየቀኑ አነባለሁ፤ እንደዛም ሁኖ ካልገባኝ አሁን ቴክኖሎጂው በጃችን በመሆኑ ኢንተርኔት ላይ በመፈለግ ሪፈረንስ መፅሐፎችን እጠቀማለሁ።

በዚህ መሃል ከተማሪዎች ‹‹ምንድነው ሁሌ ማጥናት›› የሚሉ ማዘናጊያዎች፤ ወደ ላይበራሪ ስሄድ ሌሎች ወደ ከተማ ለመዝናናት የሚወጡ ተማሪዎች ስመለከት የመረበሽ ስሜት ቢኖርም ከፍተኛ ውስጤት አምጥቸ ለመጨረስ አልሜ እራሴን ስላሳመንኩት መቋቋም ችያለሁ።

የልጅነት ምኞቴ ዶክተር መሆን ቢሆንም አሁን በተመረቁኩበት ሙያ ወደፊት የሚያስኬዱ ደረጃዎችን ሁሉ በመማር ለሀገሬ ባገለግል ደስ ይለኛል።

በተለይም ገጠራማ ቦታዎች ላይ የማህበረሰቡ ችግር የጎላ መሆኑን በልምምድ ጊዚያት የተመለከትኩ

ስለሆነ በሙያየ ብሰራ ውጤታማ ከመሆን ባሻገር ብዙ የተቸገሩ ሰዎችን በመረዳ ለሀገሬ ትልቅ አስተዋፆ ማድረግ እችላለሁ ብየ አምናለሁ።

አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ት ቤት ላሉ ተማሪዎች የማስተላልፈው መልዕክት ጊዜያቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ እና አላማን ከሚያዘናጉ ነገሮች ሊቆጠቡ ይገባል። በተለይ ሴት ልጅ ለጉዳት የመጋለጥ ዕድሏ ከፍተኛ በመሆኑ የራሷ ግብ ሊኖሯት ይገባል። አንድ አንድ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲ ሲመጡ ቤተሰብን የሚረሱት ነገር አለ።

በፊት የተሻለ የትምህርት አቀባበል ኑሯቸው ዩኒቨርሲቲ ከገቡ በኃላ የመዘናጋት ነገር እናይባቸዋለን፤ ነገር ግን መሆን ያለበት ቤተሰብ

ወደ ገጽ 5 ዞሯል




ራሄል ከሜዳሊያ ሽልማት በኋላ ከዩኒቨርሲቲው ፕሬዜዳንት ዶ/ር ፍሬው ተገኘ ጋር

## እንኳን ደስ አለን!

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ትምህርት ቤት በ2014 ትምህርት ዓመት በጤና ሚኒስቴር የስፔሻላይዜሽን መግቢያ ፈተና (ERMP) ወስደው ያለፉ 118 ረዚደንት ሐኪሞችን ከመጋቢት ወር ጀምሮ የተቀበለ ሲሆን ይህም ከጥቁር አንበሳ እና ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታሎች በመቀጠል 3ኛዉ ከፍተኛው የቅበላ አቅም ያደርገዋል።

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ተመራቂ ሐኪሞች በመግቢያ ፈተናው (ERMP) መሰረት ለስፔሻላይዜሽን የማለፍ ምጣኔ ከመንግስት ሕክምና ትምህርት ቤቶች ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመቀጠል 2ኛ ደረጃ ላይ ናቸው።



